1227. **ጥቅሜ - ጥቅማቸው**
አገልጋዬ፣ የሚረዳኝ ...።
ጥቅማቸው ፤ አገልጋያቸው ...።
ያባት ስም ብዙነኽ ቢል ይገጥማል።

1228. **ጥበበ**
ጠቢብ ፣ ብልህ፣ ዐዋቂ፣ ፈላስፋ፣ አስተ
ዋይ ማለት ነው (ኢር. 9፥23 ፤ ምሳ. 1፥7)።
ያባት ስም ሲራክ ቢል ይገጥማል።
**ጥበቡ - ጥበብ - ጥበብነኽ**
**ጥበበ ሥላሴ** ክርስትና ስምን ተመልከት።

1229. **ጥንቅሼ - ጥንቅሹ- ጥንቅሽ**
የኔ ማር፣ የኔ ጣፋጭ ማለት ነው።
ማር ማር የሚል ጣፋጭ የዘንጋዳ ፣ የማ
ሽላ አገዳ። ሸንኮራ ማለት ነው።
ያባት ስም ጣዕሙ ቢል ይገጥማል።

1230. **ጥዑመልሳን**
ደስ የሚያሰኝ ድምጽ፤ ጥዑም ዜማ ።
ያባት ስም ያሬድ ቢል ይገጥማል።
**ጥዑማይ - ጥዑሜ - ጥዑም**

1231. **ጥጋቡ**
በመብል በመጠጥ የሆድ መሙላት ...።
ሀብት ፣ ኃያልነትን ፣ እልበማ ባይነትን
ያመለክታል ። እንዲሁ ዘመነ ጥጋብን
ያመለክታል (መክ. 5፥12)።
ያባት ስም ተሰማ ቢል ይገጥማል።
**ጥጋቤ - ጥጋብ - ጥጋቦ**

1232. **ጦብያ - ጦብያው**
ማስፈያ፣ መልክ መልካም ማለት ነው።
እናንተ የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት ሆይ እኔ
ጥቁር ነኝ፤ ነገር ግን ውብ ነኝ።
(ማኃ. 1፥5)።

ከእስራኤል ወገን የተወለደ የገባኤል ልጅ
የጦቢት ልጅ ጦቢያ ይባል ነበር ጻድቅ
እና ቸር የነበረ ሰው ነው (ጦቢ.1፥1 ፤ 14
፥4 ፤ ንሀ. 2፥10)።
**ጦቢት** =ደግ፣ ጻድቅ የሚያምር ማለት ነው።

1233. **ጦና** (ዶር)
አሸናፊ ማለት ነው።
በዚህ ስም የሚታወቁት ጦና ጋጋ ናቸው።
ካዎ ጦና 21ኛው የወላይታ ንጉሥ ነበሩ።

1234. **ጥግነህ - ጥጉ**
ቦታን ያመለክታል ...። ታቹን፣ በሥር፣
ወደ ሰው መጠጋት፣ ጥግ ማድረግ ።
ያባት ስም ይቁም ቢል ይገጥማል።

**ጨ**

1235. **ጨመረ - ጨምር - ጨምሩ**
አከለ፣ ደባለቀ፣ ቀላቀለ ...።
ያባት ስም በረከት ቢል ይገጥማል
**ጨምረው - ጨመደ - ጨመዲ**
**ጨመዳ - ጨመድባ - ጨሙ**

1236. **ጨቡዴ**
ጨባጭ ማለት ነው።
ኀይለኛ ጠንካራ ጉልበተኛ ማለት ነው።

1237. **ጨነቀው - ጨነቀ**
ከችግር የተነሳ የሚሰየም ስም ነው።
ጠበበው ቸገረው፣ አወከው (ኢሳ.63፥9)።
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።

1238. **ጫላ** (ኦሮ.) – **ጫልቺሳ**
በለጠ ማለት ነው። **ጫሌ - ጫሊሳ**

1239. **ጫንያለው – ጫኔ - ጫንዬ**
ያባት ስም ኀበዜ ቢል ይገጥማል።



**- ጴ -**

1240. **ጴጥሮስ** (ግሪ)
መሠረት ወይም አለት ማለት ነው። ከዐ
ሥራ ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ በመጀመ
ሪያ ስምዖን ተብሎ ይጠራ የነበረው ነው።
ጌታም የቅጽል ስም ጴጥሮስ ነኸ ብሎ
ጠራው (ማር. 3፥16 ፤ ዮሐ.1፥43) ።

1241. **ጳውሎስ** (ግሪ)
ታናሽ ዐጭር እና ምርጥ ማለት ነው የዕብ
ራይስጥ ስሙ ሳውል ነበር፤ በሮማዊ ስሙ
ጳውሎስ ተብሎ ተጠራ (የሐ. ሥራ 13፥9)

**- ጸ -**

1242. **ጸበሉ** (ጠበሉ)
ያባት ስም መድኃኒት ቢል ይገጥማል።
**ጠበለማርያም - ጠበሌ**

1243. **ጸደቀ** (ጠደቀ)- **ጻድቅ**
አንዱ ጻድቅነትን፤ ኹለተኛው ትርጉም
በቀለ ማለት ነው። **ጻዲቄ - ጻድቃን**
የክርስትና ስም ወልደ ጻድቅ የኾናል።
ያባት ስም እትክልቴ ቢል ይገጥማል።

1244. **ጸዳሉ - ጸዳል - ጸዳለ**
ብርሃን ወይም የብርሃን ፍንጣቂ ጮራ
ወጸዳሉኒ ከመ ብርሃን ውእቱ። ትርጉም፤
**ጸዳሉም** እንደ ብርሃን ነው።
(ዕን. 3፥4 ፤ ኢሳ. 59፥9 ፤ አሞ. 5፥20)።

1245. **ጸገየ** (ግእ) - **ጽጌ**
አበበ ፣ አፈራ ማለት ነው።
በለስ ወአውፅአ ሠርጸ፤ አውያን ጸግዩ ፤
ወወሀቡ መዐዛ። ትርጉም፤ በለሱ ጐመራ
ወይኖችም አበቡ መዓዛቸውንም ሰጡ
(ማኃ. 2፥6(13))።

1246. **ጸጋዬ** (ግእ) **ጸጋ**
ጸግወ ሰጠ ለገሰ መጸወተ ካለው የግእዝ
ግስ የወጣ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ
(ጸጋ) ይባላል። ለኹሉም የሚሰጥ የመን
ፈስ ቅዱስ ስጦታ አለ። ወይም ጸጋ መን
ፈስ ቅዱስ (የሐ. ሥራ 2፥8)።
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዱ ደራሲ ጸጋ
ዬ ገብረ-መድኅን ናቸው። አባታቸው ሮባ
ቃቤባ እናታቸው ወይዘሮ ፈለቀች ዳኜ
ይባሉ ነበር ። **ጸጋቸው - ጸጋነኽ**
**ጸጋኹኔ - ጸጋኹን - ጸጋሕይወት**
**ጸጋዓለም - ጸጋለበሰ - ጸጋውብዙ**
**ጸጋመስቀል- ጸጋመላይ- ጸጋማርያም**
**ጸጋሰጠኝ - ጸጋሥላሴ - ጸጋብርሃን**
**ጸጋእምላክ - ጸጋኪሮስ - ጸጋው**

1247. **ጸጥታ**
እርጋታ፣ ዝምታ፣ ሰላም ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

1248. **ጽዱነኽ** (ጥዱነህ)
የጸዳ ፣ ንጹሕ ማለት ነው።
ያባት ስም የሉልወርቅ ቢል ይገጥማል።

1249. **ጽጌ**
ሽታው ደስ የሚል አበባ ።
ወከመ ጽጌ ገዳም ከማሁ ይፈሪ ። ትር
ጉም፤ እንደ ዱር አበባ እንዲሁ ያብባል
(መዝ. 92፥15፤ መኃ.2፥12 ፤ ኢሳ. 35፥1)።

**- ፀ -**

1250. **ፀሐይ - ፀሐዩ - ፀሐዬ**
ቀንና ሌሊት ጊዜያትና አቅጣጫዎች የሚ
ታወቁትና የሚለዩት በፀሐይ ነው
(ዘፍ. 1፥14–16)።

1251. **ፀምሩ - ፀምረ** (ግእ)
ፀምር፤ ለምድ የበግ ጸጉር፤ የሐር ባዘቶ።
መሰክ ማለትም ይኾናል (መሳ. 6፥36)።

ወ

ያባት ስም ጌዴዎን ቢል ይገጥማል።
**ፀምረ ድንግል** ክርስትና ስምን ተመልከት።

## - ፌ -

1252. **ፌለቀ**
መነጨ፣ ወጣ፣ በራ፣ አንጸባረቀ...።
ያባት ስም ቢላይ ቢል ይገጥማል።

1253. **ፌለገ** (ግእ)
የወንዝ የምንጭ ውሃ ማለት ነው።
ፌለገ ጢሮስ ፤ ፌለገ ዮርዳኖስ ይላል።
ፌለገ እግዚአብሔር ምሉእ ማያተ። ትር
ጉም፤ የእግዚአብሔር ወንዝ ውሃን የተ
ሞላ ነው (መዝ. 64(65)፥4)።
ያባት ስም ዮርዳኖስ ቢል ይገጥማል
**ፌለገሰላም - ፌለጉ ፌለገጥበብ** (ስም)
**ፌለገብርሃን ፌለገሕይወት** ክርስትና ስም

1254. **ፌረደ – ፌረደኝ - ፌረጀ**
ዳኝነት አየ፣ በየነ ...።
ያባት ስም በፈቃዱ ቢል ይገጥማል።
**ፌረጂ - ፌረጂው - ፌረጅ - ፌረጆ**

1255. **ፌቀደ - ፍቃደ**
አሰበ፣ ከጀለ፣ ወደደ፣ አየ፣ ተመለከተ፣
አስተዋለ፣ ጎበኘ ማለት ነው።
ያባት ስም በለጠ ቢል ይገጥማል።
**ፌቀደልኝ - ፌቃዱ - ፌቃደ**
**ፌቃዱነኽ - ፌቃዴ - ፍቃደ ሥላሴ**
**ፌቃደ እምላክ** ክርስትና ስም።

1256. **ፌይሳ** (ኦሮ . ጉራ)
ፌወሰ ፤ አዳነ ማለት ነው።
**ፌየራ** (ጉራ)**- ፌያ - ፌየዱ**

1257. **ፌጠነ - ፌጠኑ - ፌጣን**
በመኼድ ፤ በመናገር ፤ በማንኛውም
ጉዳይ ቸኰለ። ቀለጠፈ፣ ከዝግታ ከቀስታ
ተለየ። ታላቁን ተከትሎ ቶሎ ተወለደ።
ያባት ስም ንጋቱ ቢል ይገጥማል።

1258. **ፊልጶስ**
ፈረሶችን የሚወድ ጋላቢ ማለት ነው ወንድ
ሞችን የሚወድ ሊኾን ይችላል ከዐሥራ
ኹለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው (ማቴ. 10፥3
፤ የሐ. ሥራ 6፥3) ። በቅዱስ መጽሐፍ
ወደ አምስት ሰዎች ተጠርተውበታል።

1259. **ፊደሉ - ፊደል**
የእሱ ፊደል ማለት ነው።
ያባት ስም ጀመረ ቢል ይገጥማል።

1260. **ፊጣ** (ኦሮ)
ጨረሰ ማለት ነው። **ፊጤ**

1261. **ፋሲል** (ግሪ)
ፋሲል ማለት የንጉሥ ልጅ ማለት ነው።
በዚህ ስም ዐፄ ፋሲል ስመ መንግሥታ
ቸው ሥልጣን ሰገድ የተባሉት ተጠርተው
በታል። 36 ዓመት ኢትዮጵያን አስተዳድ
ረዋል። በግራኝ አሕመድ የፈረሰውን የአ
ክሱም ቤተክርስቲያን ሕንፃን አሰርተዋል።

1262. **ፋሲለደስ**
በሰንክሳር ከታወቁት አንዱ ሰማዕት ነው።
የዐፄ ኢያሱ (አድያም ሰገድ) ልጅ። የዐፄ
ባካፋ (መሲሕ ሰገድ) ወንድም ፋሲለደስ
ይባላል።

1263. **ፋሲካ - ፋሲካው - ፋሲኬ**
ከትንሣኤ በዓል እስከ ዳግም ትንሣኤ
ያለው ጊዜ በዕብራይስጥ ፓሲካ ይባላል።
የደስታ ጊዜ፤ ደስታ ነው ለማለት ፋሲካ
ነው ይባላል። ፋሲካ ማለት ዐለፈ ማለት
ነው (ዘጸ. 12፥1)።



1264. **ፋንታዬ**
የኔ ድርሻ ፤ ለኔ የሚሰጠኝ ...።
ድርሻ፣ ዕድል፣ ተራ፣ ምትክ፣ ለውጥ
ማለት ነው (ዘጸ. 35፥5፤ ኢሳ. 57፥6 )።
**ፈንታኹን(ፋንታሁን) - ፋንታው**
**ፋንታዬ - ፈንታይ - ፋንቴ**

1265. **ፋኖሴ - ፋኖስ - ፋኑስ**
ብርሃኔ፣ ጭለማን የሚገልጥልኝ ...።
ከብርጭቆ እና ከመስታወት የተሰራ ፓኖስ
ወይም ወፍራም ጧዋፍ (ኢሳ. 62፥1 ፤
ዮሐ. 18፥3)።

1266. **ፋኑኤል** (ዕብ)
ከነገደ አሴር የኾነችው ነቢይት ሐና አባ
ቷ ፋኑኤል ይባላል (ሉቃ. 2፥10)።
ከሊቃነ መላእክት አንዱ ፋኑኤል በመ
ባል ይታወቃል (ሄኖ. 10፥15)።

1267. **ፍሬ - ፍሬሰላም**
አበባ ካበበ በኋላ የሚገኝ ...።
**ፍሬሰው - ፍሬዘር - ፍሬሠናይ**
**ፍሬኹን - ፍሬወርቅ - ፍሬው**
የክርስትና ስሞች ተመልከት።
**ፍሬ ኢየሱስ - ፍሬ ድንግል**
**ፍሬ ስብሐት - ፍሬ ማርያም**
**ፍሬ ሰንበት - ፍሬ እግዚአ**

1268. **ፍሬምናጦስ** (ግሪ)
በቅዱስ አትናቴዎስ የተሾሙ የመጀመሪ
ያው የኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ናቸው ። ከጵ
ጵስና በፊት በግሪክ ስማቸው ፍሬምናጦስ
በመባል ይታወቁ ነበር። **ከሣቴ ብርሃን -**
**ሰላማ** የሚለውን ተመልከት።

1269. **ፍላጎቴ - ፍላጎት**
የኔ ፍላጎት ማለት ነው።
ያባት ስም አለነ ቢል ይገጥማል።

1270. **ፍርዳወቅ (ፍርድዐወቅ)**
ዳኝነት፣ መዳኘት ዐወቀ ማለት ነው።
ያባት ስም በየነ ቢል ይገጥማል።

1271. **ፍሥሓ** (ግእ)
ደስታ ፤ ሰላም ማለት ነው።
ያባት ስም ለይኩን ቢል ይገጥማል።
**ፍሥሓዬ - ፍሥሓይ- ፍሥሓ ጽዮን**

1272. **ፍቅሬ - ፍቅረ ማርያም**
የማፈቅረው፣ የምወደው ...።
ያባት ስም ዐየለ ቢል ይገጥማል።
**ፍቅረዓለም - ፍቅሩ - ፍቅር**
**ፍቅረሕይወት - ፍቅራይ - ፍቅረ**
**ፍቅረሰላም - ፍቅርዐዲስ - ፍቅርዬ**

1273. **ፍትሐነገሥት** (ግእ)
የቤተ ክርስቲያን እና የመንግሥት መተዳ
ደሪያ ሕግ ነው።
ያባት ስም ሕጉ ቢል ይገጥማል።
**ፍትሕዓለም - ፍትሕ እምላክ**
**ፍቱንወርቅ - ፍትሕ - ፍትሕና**

1274. **ፍኖተጽዮን** (ግእ) **- ፍኖተ**
የጽዮን መንገድ ማለት ነው።
**ፍኖተሰላም**

1275. **ፍጹም – ፍጹምወርቅ**
ምሉእ የኾነ ጉድለት የሌለበት
(ዘዳ. 25፥15፤ ዕብ. 5፥14፤ ያዕ. 1፥24)።
ያባት ስም ክብረት ቢል ይገጥማል።
**ፍጹምብርሃን - ፍጹማዊ**

ወ

11. **ለባዊት** (ግእ)
ልብ ያደረገች፤ ያስተዋለች፤ የማስታወስ ችሎታ ያላት ማለት ነው።

12. **ለቤዛ - (ለቤዛዓለም)**
ምሳሌ፣ በይሥሐቅ ምትክ የተሠዋ በግ። (ዘፍ. 22፥13 ፤ ማቴ. 26፥28)
ያባት ስም መድኅኒት ቢል ይገጥማል።

13. **ለታሪክ**
ይህ ኹሉ ያልፍና ለታሪክ እናውጋው።
ያባት ስም ተመቸ ቢል ይገጥማል።

14. **ለኹሉም - ለኹሉ**
ለብዙዎች መኾን ።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።

15. **ለወግነሽ**
አለኝ ብዬ ለመናገር ፤ ለማውጋት
ያባት ስም ጌጤ ቢል ይገጥማል።
**ለወግ - ለወግሰጠኝ - ለወጌ**

16. **ለወጠችኝ**
ከወጣትነት ዘመን ልጅ ሲወለድ መለወጥ፤
ያባት ስም በፍቅሩ ቢል ይገጥማል።

17. **ለውዘገነት**
የገነት ፍሬነሽ ለማለት ነው።
(ለውዝ ጣፋጭ ፍሬ ፤ ቀይና ነጭ አበባ ያለው ። የኮክ ዛፍን የሚመስል ተክል። (ዘፍ. 43፥11 ፤ መክ. 12፥5፤ ኤር 1፥11)
ያባት ስም ታከለ ቢል ይገጥማል።

18. **ለዓለም**
እንትሙ ለዓለም ብርሃኑ። ትርጉም ፤ የዓለም ብርሃን ናችሁ (ማቴ. 5፥14)።
ያባት ስም ብርሃኑ ቢል ይገጥማል።

19. **ለዕለት**
ማምሻም ዕድሜ ነው እንደሚባለው።
ያባት ስም አገኘኹ ቢል ይገጥማል።

20. **ለገሠች**
ሰጠች ፤ ቸርነት አደረገች
ያባት ስም ዕንቍብርሃን ቢል ይገጥማል።
**ለገሡኝ - ለጋሥ - ለጋሥነሽ**

21. **ለጋነሽ**
ለምለም ያልጎመራ (ያልበሰለ)።
ያባት ስም እሸቴ ቢል ይገጥማል።
**ለጋወርቅ - ለጋዓለም**

22. **ሉሲት (ሉል)**
የከበረ ድንጋይ ዕንቍ ማለት ነው።
(ዘፍ. 2፥12)
ያባት ስም ድንቅነህ ቢል ይገጥማል።
**ሉልወርቅ - ሉልሸት - ሉልዬ**
**ሉልዓየኹ (ሉላየኹ) - ሉሉ**

23. **ሊሊ** (ግሪ)
ከግሪክ የተወሰደ ቃል ነው። ከምድር የተ ጣበቀች ትንሽ አበባ፤ እቴጌ ጣይቱ ፀዲስ አበባ አገኘኹ ያሏት አይነት፤ ሜዳ ላይ የምትበቅል ደስ የምታሰኝ (ማቴ. 6፥28)።
**ሊሊት - ሊሊያና**

24. **ላንቺይደሩ**
ይገዙልሽ ፣ ይታዘዙልሽ
ያባት ስም በእምነት ቢል ይገጥማል።

25. **ላመስግን — ላመስግናት**
በተሰጠኝ ስጦታ ፣ በረከት ላመስግን።
ያባት ስም ይበቃል ቢል ይገጥማል።



26. **ላቀች**
ከኹሉም በለጠች ፣ ተሻለች ...።
ያባት ስም በሐርወርቅ ቢል ይገጥማል።
**ላቁ - ላቁብሽ**

27. **ላንቻደላኹ — ላንቺበል**
ኹሉን በመተው፤ አንድ ወገን ኾንኩ ...።
ያባት ስም በፍርዱ ቢል ይገጥማል።

28. **ላዋይሽ — ላዋይ**
ላጫውትሽ፤ የሚነገር ምስጢር አለኝ...።
ያባት ስም መስከረም ቢል ይገጥማል።

29. **ላዩሽ - ላየሽ**
የሚመለከትሽ ኹሉ፤ ውበትሽን፣ ሞያሽን ሀብትሽን... ።
ያባት ስም እማረ ቢል ይገጥማል።

30. **ልመንሽ**
ማመን ፣ መታመንን ያመለክታል።
ያባት ስም በሐርወርቅ ቢል ይገጥማል።

31. **ልበብርሃን**
አእምሮዋ ብሩህ የኾነ። ንቁ የነቃች።
ያባት ስም ቢጠኝ ቢል ይገጥማል።

32. **ልባሟ**
አስታዋሽ ፣ የተነገረውን ፣ የተሠራውን የማትረሳ። **ልባዊት — ልቤነሽ**
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

33. **ልብሰወርቅ**
የወርቅ ልብስን የተላበሰች።
ያባት ስም ፀዲሉ ቢል ይገጥማል።
**ልብሰቃል - ለብሰተ - ልብሰፀሐይ**
**ልብስነሽ - ልብሴ**
**ልብሰ ማርያም** ክርስትና ስም።

34. **ልንገርሽ**
ምስጢር ወይም ያየኹትን ?
ያባት ስም ቡዙአየሁ ቢል ይገጥማል።

35. **ልከየለሽ**
የሚወዳደርሽ ፣ የሚተካከልሽ የለም።
ያባት ስም አጥናፍዓለም ቢል ይገጥማል።
**ልክምየለሽ - ልኬ - ልክዬ**
**ልኬወርቅ - ልኪቱ - ልኬነሽ**
**ልክአለሽ - ልክነሽ**

36. **ልዕልተወይን**
ባሕረ ሐሳብን ወይም የዘመናትን አቆጣ ጠር ያዘጋጀ ዲሜጥሮ ከእንቀ ልጅ ጋር 48 ዓመት በንጽሕና በአንድ አልጋ ላይ ኖረዋል። የንጽሕና የድንግልና ምሳሌ ነች።
**ልዕሊባ - ልዕልተ - ልዕልተወርቅ**
**ልዕልቷ - ልዕልቲ - ልዕልና - ላዕላይ**

37. **ልያ** (ዕብ.)
የላባ ታላቅ ልጅ የራሔል እኅት ለያዕቆብ የተዳረች ነች ። የመጀመሪያዋ የያዕቆብ ሚስት ነች (ዘፍ. 29፥16 - 30)።

38. **ልይሽ - ልያት**
ናፍቆትን ፣ መጓጓትን ያመለክታል።
ያባት ስም ወዳጄ ቢል ይገጥማል።

39. **ልዩወርቅ**
ከማንም የማትተካከል ተወዳዳሪ የሌላት።
(ዘፍ. 2፥12)
ያባት ስም በትዛዙ ቢል ይገጥማል።
**ልዩሥራ - ልዩነሽ - ልዩ - ልዩፋንታ**
**ልዩጌጥ - ልዩዜና - ልዩዝና**

ሌ

40. **ልድያ** (ግሪ)
ልድያ በተባለች አገር ያለች ሴት ልጅ ማለት ነው። ልድያ የሚባለው ቦታ የሚገኘው በፊልጲስዩስ በእስያ ክፍል ነው። በመጀመሪያ በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ክርስትናን ተቀብላ የተጠመቀች ሀብታም የትያጥሮን ተወላጅ ነች (ሐዋ.ሥራ 16፥14-15፥40)።

41. **ልጃለም (ልጅዓለም) – ለጃምር**
ደስታን የምትሰጥ ።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

42. **ሎሚ – ሎሚናት - ሎሚቱ**
መዓዛው ጥፍጥ ፤ የሚመጠጥ ኮምጣጥ የሚል ተወዳጅ ፍሬ ነው።
ያባት ስም ፍሬሰላም ቢል ይገጥማል።

43. **ሎዛ (ዕብ.)**
የለውዝ ቦታ (የረድኤት ቦታ) ማለት ነው። ስመ ሀገር ፤ በኤፍሬም ድርሻ ውስጥ ያለች (ዘፍ. 28፥10)፤ ያዕቆብ በመንገድ ሲጓዝ አደረባት ፤ በዚህች ቦታ ሕልም አለመ። ሲነጋም ቦታዋን ቤተል ብሎ ሰየማት ።

## - ሐ -

44. **ሐመር** (ግእ) - **ሐመረ**
መርከብ ፤ ሐመረ ኖኅ ትርጉም የኖኅ መርከብ ማለት ነው ። (ዘፍ 6፥14)
የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ። ሐመረ ሥላሴ ሐመረ ድንግል ተብሎ ክርስትና ስም ይሰየማል ።

45. **ሐመልማል** (ግእ)
ለምለም ቡቃያ ሣር፤ ቅጠል፤ ተክል፤ ዛፍ ወሐመልማለ ለቅኔ አኻለ እመሕያው ። ትርጉም ለምለሙን ለሰው ልጆች ጥቅም (ዘፍ.1፥11፤ 2፥5 ፤ መዝ.103 (104) ፥13)
በዚህ ስም ብዙ ኢትዮጵያውያን የጠሩበታል። **ሐመልማለ ወርቅ**
ክርስትና ስም **ሐመልማለ ድንግል** ይባላል።

46. **ሐረገወይን** (ግእ)
ይህ ስም ቅድስት ድንግል ማርያምን ያመለክታል። እሷ በሐረግ ስትመሰል ወይን የጌታ ምሳሌ ነው ።
**ሐረግነሽ - ሐረጊቱ - ሐረጊት**
**ሐረጌ - ሐረግ - ሐረግሽወርቅ**
**ሐረጓ - ሐረገወይኒ (ትግ)**

47. **ሐሤት** (ግእ)
ታላቅ ደስታ፤ ደስ መሰኘት ማለት ነው። በትፍሥሕት ወበሐሴት ። ትርጉም፤ በደስታና በሐሴት (ሉቃ. 10፥21 ፤ ዮሐ. 8፥56)።

48. **ሐሳብነሽ**
ከመወለድ በፊት በሐሳብ የነበረች።
ያባት ስም **መልካሙ** ቢል ይገጥማል።
**ሐሳቤ - ሐሳበወርቅ - ሐሳቧ**

49. **ሐብለወርቅ**
በአንገት ላይ የሚደረግ ። ወዳጅነትን ያመለክታል። (ያንገት ወርቅ)
ያባት ስም **ማተቤ** ቢል ይገጥማል።

50. **ሐኪምነሽ - (ዐኪምነሽ)**
የምትፈውስ ፣ ያዳነች ማለት ነው።
(ኤር. 8፥28)
ያባት ስም **መድኅኔት** ቢል ይገጥማል።



51. **ኅዋ** (ዐረ. ኦሮ) ንፋስ ማለት ነው።
**ኅዋ** (ግእ) ጠፈር ማለት ነው።

52. **ሐዊ** (ኦሮ) ምኞት ማለት ነው።

53. **ሐውልቴ**
መታሰቢያ ፤ ምስክር ማለት ነው።
(ዘፍ. 28፥18 ፤ 31፥45-54 ፤ ኢያ. 4፥1-9 ፤ 24፥27 )።
ያባት ስም **መታሰቢያ** ቢል ይገጥማል።
**ሐውልት - ሐውልቲ** (ትግ)

54. **ሐይቀብርሃን** (ግእ)
ብርሃን የኾነ ሐይቅ ማለት ነው።

55. **ሐይነሽ** (ጉራ)
አዋቂ (ብልህ) ነሽ ማለት ነው።

56. **ሐዲስ** (ግእ) **ሐዲሴ**
ዐዲስ ማለት ነው። (ኤር. 31፥31)
**ሐዳሱ- ሐድሽ** (ትግ)
የሸቱ ቅጠል ስም ። ሴቶች ከቅቤ ጋር የሚቀቡት፣ የዳቦ ማጣፈጫ በዐማርኛ ዐደስ የሚባለው ማለት ነው።

57. **ሔለን**
የንጉሥ የቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት እሌኒ በምዕራባውያን ሔለን በመባል ትታወቃለች (255-330 ዓ.ም)። ገጽ 196 ቁ. 625

58. **ሔዋን** (ዕብ.) - **ሔዋኔ**
የሕያዋን ኹሉ እናት ማለት ነው ፤ (ዘፍ. 3፥15 ፤ 1ኛጢሞ. 2፥14) ። በዚህ ስም ብዙዎች ይጠራሉ።

59. **ሕልመ**
በሕልም የታየች ሊኾን ይችላል።
(ዘፍ. 20፥3 ፤ 28፥12 ፤ 37፥5-11 ፤ 40፥5 ፤ ዳን. 2፥25 ፤ ማቴ. 1፥20 ፤ )
ያባት ስም **ዮሴፍ** ቢል ይገጥማል።
**ሕልምነሽ - ሕልሙነሽ- ሕልሜ**

60. **ሕንደኬ** (ግሪ) (**ኄርሳሞት**)
በ35 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ንግሥት ስሟ **ሕንደኬ** ወይም **ኄርሳሞት** ይባል ነበር ። ጃንደረባው ወደ ኢየሩሳሌም ተልኮ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ትዛዝ ፊልጶስ አጠመቀው። የክርስትናንም ሃይማኖት ለቤተ መንግሥቱ አስተዋወቀ (የሐ.ሥራ 8፥27)።

61. **ሕዝባለም**
ያባት ስም **ተዋሕዶ** ቢል ይገጥማል።
**ሕዝባየኹ - ሕዝባዊት - ሕዝባንቺ**

62፡ **ሕይወት**
ተሐድሶ፤ መዳን፤ ጤና ያመለክታል ፤ ሕይወት ኹሉ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ነው። የነፍስ ሕይወት ፤ የሥጋ ሕይወት አለ (ዘፍ.2፥7 ፤ ዘፍ. 6፥17 ፤ ሮሜ.8፥6)።
**ሕይወተ - ሕይወትነሽ - ሕይወቴ**

63. **ሕገሥላሴ - ሕግነሽ**
ለማድረግ የሚያዝ ፤ ከማድረግ የሚከለክል ውሳኔና ሥርዓት (ዘጸ. 20፥1)።
ያባት ስም **በእምነት** ቢል ይገጥማል።
**ሕጋችን - ሕገእግዚአብሔር**

## - መ -

64. **መለሰች**
አዳነች፤ አተረፈች ማለት ይኾናል። እንዳይኼድ ወደቀድሞው ቦታው እንዲመለስ አደረገች። **መለሱ - መልሺው**

141. **ማኅተመ**
ምልክት አደረገ ማለት ነው።
የውል የማንኛውም ነገር መተማመኛ ፤ ስም የተቀረጸበት ሊኾን ይችላል። ፈርኦን ለዮሴፍም በአንገቱ የወርቅ ዝርግፍ (ማኅተብ) አደረገለት (ዘፍ. 41፥42 ፤ ኤር. 32፥10–14)። **ማኅተበ** - (**ማኅተቤ**) **ማኅተመ ስላሴ** ክርስትና ስም።

142. **ማኅቶተ** (ግእ) **ማኅቶት**
ብርሃን ማለት ነው ።
ያባት ስም **ዓለም ቢል** ይገጥማል።

143. **ማኅደረ** (ግእ)
ማደሪያ ማለት ነው ። ማኅደረ ለመንፈስ ቅዱስ ። ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ።
**ማኅደረ ማርያም** ክርስትና ስም።

144. **ማኅፈድ** (ግእ)
ግንብ፣ መከለያ፣ አንባ ማለት ነው።
አነ ቅጽር፤ ወአጥባትየ ከመ ማኅፈድ።
እኔ ቅጥር ነኝ ጡቶቼም እንደ ግንብ ናቸው (መሐ. ዘሰሎ. 5፥6(10)።
ያባት ስም **ነበልባሉ ቢል** ይገጥማል።

145. **ማናኸሉሽ** (**ማንአህሉሽ**)
በሙያ፣ በሥራ፣ በውበት ማለት ነው።
ማንም አይደርስብሽም ለማለት ነው።
ያባት ስም **በዕውቀት ቢል** ይገጥማል።
**ማናልምሽ - ማናለብሽ - ማናየሽ**
**ማንተጋፍቶሽ - ማንተዳፍሮሽ**
**ማንያኸልሻል - ማንይሉሻል**
**ማንያዝሻል - ማንይንካት**
**ማንደፍሯት - ማንጠግቦሽ**

146. **ማንቤት**
የሚተካከልሽ ፣ የሚደርስብሽ ...።

147. **ማእዜ** (ግእ)
ምንጊዜ፤ በምን ሰዓት ማለት ነው።
ማእዜ እበጽሕ ወእሬኢ ገጸ ለአምላኪየ። ትርጉም፤ መቼ እደርሳለኹ ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለኹ?
(መዝ. 41፥2)።

148. **ማክዳ**
የኢትዮጵያ ንግሥት ወይም የሳባ ንግሥት ነች ። ዘሯ ከኩሽ ልጅ የወረደ ነው ይባላል። አዜብን - ሳባን ይመልከቱ።

149. **ማዕረጓ - ማዕረጌ**
ክብሯ፤ ክብሬ። ከፍ ከፍ ያደረገችኝ።
ያባት ስም **አንተነህ ቢል** ይገጥማል።

150. **ማዕዶት** (ግእ)
ማዶ ፣ መሻገሪያ፤ ከሞት ወደ ሕይወት መሻገርያ ማለት ነው ። የትንሣኤ ሰኞ ቀን ማዕዶት ይባላል።

151. **ማዘንጊያ - ማዘንጊያሽ**
ማስረሻ ማለት ነው።
በዚህ ስም የሚታወቁት የአለታ ገብረሃና ባለቤት ወ.ሮ ማዘንጊያ የሚባሉት ናቸው፤
ያባት ስም **ፀየስ ቢል** ይገጥማል።

152. **ሜላተ** (ግእ) – **ሜላተወርቅ**
ነጭ የሐር ግምጃ ማለት ነው።
መንበሩ ዘሜላት። ትርጉም፤ ዙፋኑ የቀይ የነጭ ሐር (መሐ. ዘሰሎ. 3፥5)። **ሜላት ሜላተ ሥላሴ፤ ሜላተ ድንግል** (ክር)

153. **ሜሮን** (ግሪ)
ቅባ ቅዱስ ከበለሳ እና ከዕጣን ከልዩ ልዩ እንጨቶች የተቀመመ ሽቱ። ተነጥሮ የሚወጣ ዘይት ማለት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። በክርስትና ጊዜ ጳጳስ ፣



ንጉሥ፣ ቄስ ሲሾም የመቀባ ማለት ነው (ዘጸ. 30፥22 ፤ 1ኛ ዮሐ. 2፥20)።

154. **ሜቲ** (ኦሮ)
አንባሬ፣ ኈጤነሽ፣ ወርቄነሽ ማለት ነው።

155. **ምልዕተ** (ግእ) **ምልዕተ ክብር**
ክብርን የተሞላች ማለት ነው ።
ያባት ስም **ጸጋ ቢል** ይገጥማል።

156. **ምሕረት** (ግእ) **ምሕረተ - ምሕረቴ**
ይቅር መባል ፤ ርኅራኄ ፣ ቸርነት ቅጣት ለሚገባው ምሕረት ማድረግ እንዲሁም ለደካሞች ለበሽተኞች ርዳታ ማድረግ (መዝ. 50 ፤ 129፥7 ፤ ምሳ. 14፥21 )። የኪዳን ምሕረት በዐል ዕለት የምትወለድ ወይም የክርስትና ቅጽል ይኾናል።

በዚህ ስም ከተጠሩት አንዷ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ነርስ ሲስተር **ምሕረት ጳውሎስ** ይባሉ የነበሩ በጣሊያን ጊዜ በስደት ዘመን በዒ ኃይለ ሥላሴን በአስተርጓሚነት ያገለገሉ ናቸው ።
**ምሕረተ ኪዳን** ክርስትና ስምን ተመልከት።

157. **ምሥራቅ – ምሥራቄ**
እምሥራቀ ፀሐይ እስከነ ዐረብ። ትርጉም ፤ ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያ ድረስ (መዝ. 112፥3)።
ያባት ስም **በረኸን ቢል** ይገጥማል።

158. **ምሥራች**
የደስታ ወሬ፣ ነገር፣ ልጅ በተወለደና ድል በተገኘ ጊዜ፤ ሌላም ይህንን የመሰለ የሚያስደስት ጉዳይ በተገኘ ጊዜ ፤ የሚነገር ቃል በግእዝ ብሥራት ይባላል።
አብሣሪ ዐዲስ ነገርን የሚናገር ማለት ነው (ሉቃ. 1፥26 ፤ ግብ. ሐዋ. 12፥14)።

159. **ምርትነሽ**
በእጥፍ ትርፍ ማግኘት ።
ያባት ስም **በሽይበሉ ቢል** ይገጥማል።

160. **ምርቃት**
በረከት ፣ ጸጋ (ዘዳ. 20፥5)።
ባለው ላይ ተጨማሪ ስጦታ።
ያባት ስም **አገኘኹ ቢል** ይገጥማል።

161. **ምርጥነሽ - ምርጫዬ**
የተመረጠች ፤ የተለየች ፣ የተወደደች
**ምልምል** (ሮሜ. 8፥33)።
ያባት ስም **ወርቁ ቢል** ይገጥማል።

162. **ምሳሌ**
አንድን ነገር ግልጥ ለማድረግ ሲፈለግ የሚቀርብ ማስረጃ ማብራሪያ እና መግለጫ ማቅረብ ማለት ነው። ሰሎሞን ብዙ ምሳሌዎች ተናግሯል (1ኛ ነገሥ. 4፥32)።

163. **ምሳዬ**
ሆድ ባዶ ኾኖ በእኩለ ቀን የሚገኝ ...።
ያባት ስም **ደረሰ ቢል** ይገጥማል።

164. **ምስለአበባ** (ግእ) - **ምስሌ**
የአበባ ምስል ፣ አበባ የመሰለች ፤
ያባት ስም **ተውህቦ ቢል** ይገጥማል።

165. **ምስክርነሽ – ምስክር**
ስሕተት የሌለበት ማስረጃ ነሽ ፤ እንዲሁም ቃል ኪዳን ማለት ነው (ዘፍ. 31፥44 ፤ ዘዳ. 31፥19–20) ።
ያባት ስም **ዘላለም ቢል** ይገጥማል።

166. **ምስጢረ** (ግእ)
ረቂቅ ስውርና ድብቅ ሽሽግ ማለት ነው።

መግለጽ ያልተቻለ ሐሳብና ምክር ። ምስ
ጢሬ ነሽ ማለት ነው።
**ምስጢረ ሥላሴ ክርስትና ስም።**

167. **ምስጋና**
እግዚአብሔርን ሌሎችንም ፍጡራን ከፍ
የሚያደርግና የሚያከብር ቃል። ሃሌ ሉያ
ማለት ምስጋና ነው (መዝ. 111 – 117)።

168. **ምትኬ**
ቦታዬን ተክታ የምትይዝ ...።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
**ምትክነሽ - ምትኬነሽ - ምትኪ**

169. **ምቹዓለም**
የሚመች ፣ የተሳካ ፣ የተቃና ።
ያባት ስም ቢኾነኝ ቢል ይገጥማል።

170. **ምንትዋብ**
በዚህ ስም ይጠሩ ከነበሩት ኢትዮጵያዊ
የዐፄ ባካፋ ባለቤትና የዐፄ ኢያሱ
ዳግማዊ (ቋረኛው ኢያሱ) እናት
እቴጌ ምንትዋብ መንበሩ ነበሩ ። እቴጌ
ምንትዋብ ካሠሯቸው ቤተክርስቲያን የጎን
ደር ቍስቋም አንዱ ነው።

171. **ምንይሉሽ**
ያባት ስም ወርቅበዛ ቢል ይገጥማል።
ምን የሚለው ቅጽል ተጨምሮለት
**ምናለች - ምናለሽዋ - ምናሉ
ምንይሉ**

172. **ምንታምር**
እንዴት ታምር ...።
ያባት ስም ወገኔ ቢል ይገጥማል።
**ምንትችል - ምንተስኗት - ምንውዬ
ምንውዬልሽ**

173. **ምኞቴነሽ – ምኞት - ምኞቴ**
ከፍ ባለ ስሜት አንድን ነገር መሻት ፤
ሴት ልጅ ለማግኘት ሲመኙ የነበሩ ቤተሰ
ቦች ምኞታቸው ሲፈጸም የሚሰይሙት
ሊኾን ይችላል ። (1ኛ ጴጥ. 2፥2 ፤ ማቴ
13፥17)።

174. **ምክር – ምክሬ**
መከረ ከሚለው ግስ አወጣ አወረደ አሰተ
ዋለ መሰት ይኾናል ። ምክር ወሠናይት
ለኵሉ ዘይገብራ ። ትርጉም፤ (ምክር)
ለሚያደርጉት ኹሉ ደኅና ማስተዋል
አላቸው (መዝ. 110፥10)።
ያባት ስም በትዛዙ ቢል ይገጥማል።

175. **ምዕራፌ - ምዕራፍ**
ማረፊያዬ ማለት ነው።
ማረፊያ ቦታ ማለት ነው (ሉቃ. 24፥13)።

176. **ሞጣሕተ ብርሃን - ሞጣሕተ**
የብርሃን ልብስ ማለት ነው ...።
ሞጣሕት ማለት ታቦት ተሸካሚ የሚያጠ
ልቀው ልብስ ነው ። የወርቅ መርገፍ ያለ
በት፤ ዘርፍ ያለበት ቀይ ከፋይ ጎኑ ከበን
ዝር የማይበልጥ መሰቀለኛ ነው። (ቅ.ገብ)

## - ሠ -

177. **ሠላስ** (ትግ)
ሦስት ዐሥር ማለት ነው። ሦስተኛ።
የዐፄ ዮሐንስ አራተኛ የእናታቸው ስም
ሥላስ ድምፁ ይባል ነበር።

178. **ሠረገላ – ሠረገላዬ**
በኹለት ፈረስ የሚሳብ ንግሥት እና ነገ
ሥታት፤ በክብር የሚጓዙበት ። ኤልያስ
በእሳት ሠረገላ ዐረገ ይህም የእግዚአብሔ
ርን ክብር የሚያመለክት ነው።



(2ኛ ነገሥ. 2፥11) ቤትን የሚሸከም
ወራጅ ሠረገላ ይባላል (1ኛ ነገሥ. 7፥2)።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።
**ሠረገላኤልያስ - ሠረገላፀሐይ**

179. **ሠራሽ**
ፈጠረሽ ወይም እንደ ገና አበጃጀሽ
ማለት ነው። **ሠራዓለም - ሠራወርቅ
ሠራሽድንቅ - ሠራሽብዙ - ሠራት
ሠራሕይወት - ሠራሽ - ሠራንሽ**

180. **ሠርክለም** - (**ሠርክዓለም**)
ኹል ጊዜ ዐዲስ ፤ ኹል ጊዜ ደስታ
ማለት ነው። ማታ ለቀን ቀን ለማታ የማ
ትጠገብ ። **ሠርክሽት
ሠርካበባ - ሠርካዲስ - ሠርኬ**

181. **ሠናይት** (ግእ) **ሠናይ - ሠናያት**
መልካም ፣ ውብ ፣ ደግ ፣ በጎ ፣ ቅን
ደስ የሚያሰኝ የመልክ የጠባይ ተሰጥዎ ።
ሠናይ ዜና መልካም ዜና ማለት ነው።
ሠናይተ ምክረ ወጥበበ ምህረኒ፤ ትርጉም
መልካምን ምክርና ዕውቀትን አስተምረኝ
(መዝ. 118፥65)።

182. **ሠዊተ** (ዕብ. ግእ) **ሸዊት**(ትግ)
የደረሰ እሸት (ጎምር) ዛላ ዕንቡጥ ታሽቶ
ተፈልፍሎ የሚበላ የእህልና የተክል ዘር
(ዘፍ.41፥5)።
ወአርዳኢሁሰ ርኅቡ ወአኀዙ ይምሐዉ
ሰዊተ ወይብልዑ። ትርጉም፤ ደቀመዛሙ
ርቱ ተርበው ነበረና እሸት እያሹ ይበሉ
ነበር (ማቴ. 12፥1)።

183. **ሣህሏ** (ግእ) (**ሣህለ ማርያም**)
ቸርነቷ ፣ ይቅርታዋ ማለት ነው።
**ሣህሌ- ሣህለ - ሣህል - ሣህለወርቅ**

184. **ሣራ**
**ልዕልት ማለት ሲኾን ሦራ ደግሞ ልዕልቴ
ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን የአብርሃም
ባለቤት ነች፤ ባሏን አክባሪ ስለነበረች የጋ
ብቻ የፍቅር ምልክት ኾና ስትጠራ ትኖ
ራለች (ዘፍ.11፥29)።**
በዚህ ስም ከሚጠሩ ኢትዮጵያን አንዷ
**የዐፄ ኀይለ ሥላሴ ልጅ ልዑል መኰንን
ባለቤት ልዕልት ሣራ ግዛው ናቸው።**

185. **ሣሮን** (ዕብ)
ደስ የሚል የባሕር የወንዝ ዳር ሜዳ።
ረባዳ ቦታ ከኢዮጴ እስከ ቀርሜሎስ ያለ
ቦታ (ኢሳ. 33፥9፤ 1ኛ ዜና. 5፥15)።

186. **ሥሌናት** (**ሥዕሌናት**)
መልኬ፣ የምትመስለኝ፣ ውበቴ ናት ...።
ያባት ስም ውበቴ ቢል ይገጥማል።
**ሥዕሌ - ሥዕልሽ - ሥዕሉነሽ**

187. **ሥምረት** (ግእ) ሥምረተ ኪዳን
የተወደደች ማለት ነው ።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።

188. **ሥራዬ - ሥራነሽ**
እግዚአብሔር ሰውን ለሥራ ፈጠረ።
እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ወስዶ ያበጃ
ትም ይጠብቃትም ዘንድ (ይሠራ ዘንድ)
በኤደን ገነት አኖረው። (ዘፍ. 2፥15)
ያባት ስም ደባለኝ ቢል ይገጥማል።

189. **ሥነምግባሯ** (ግእ) - **ሥነ**
ሠነየ ከሚለው አማረ፣ ተዋበ ይወጣል።
ያባት ስም አማረ ቢል ይገጥማል
መልካምነት ደግነት በጎነት ማለት ነው
(መዝ. 44፥49 ፤ ሲራ. 9፥8፤ 11፥4)።
**ሥነሕይወት - ሥነፀሐይ
ሥነ ማርያም**

**ብዙወርቅ - ብዙአየን - ቡዙ**
**ብኂኙ - ብዙወርቅ - ብዙ**
**ብዙሰው - ብዙነሽ - ብዙዓለም**
**ብዙዐይኔ** (ብዙ ዐይኔ) - **ብዙዐይኔ**

371. **ብፅዕት - ብፅዐቴ - ብፅዐት**
የተባረከች ደስተኛ ማለት ነው (የሐ. ሥራ. 20፥35 ፤ ሉቃ.1፥48 ፤ ማቴ.5፥3)።
ያባት ስም ሰጦታው ቢል ይገጥማል።

372. **ቦሰና** (ኦሮ) ጫካ ማለት ነው።

373. **ቦንቱ** (ኦሮ)
የቤት እንበሳ ኩራተኛ ማለት ነው።

374. **ቦጋለች**
በኀይል በራች፣ ታየች፤ ዓይናማ መኾኗን ያሳይል።
ያባት ስም ፀሓይ ቢል ይገጥማል።

## - ተ -

375. **ተመስገንች - ተመስገን**
ምስጋናን ማግኘትን ያመለክታል ።
ያባት ስም አገኘሁ ቢል ይገጥማል።

376. **ተመቸሽ**
መደላደልን፣ መረጋጋትን ያመለክታል
ያባት ስም ሰንቄ ቢል ይገጥማል።
**ተመቸ - ተመቼ - ተመቸሻቸው**

377. **ተመኙ**
አሰቡ፣ ከጀሉ፣ ፈለጉ (1ዜና. 11፥17)።
ምኞት፣ መጓጓትን ያመለክታል።
ያባት ስም ሙሉሸዋ ቢል ይገጥማል።
**ተመኙ - ተመኙሽ - ተመኘሽ**

378. **ተሙኒ** (ጉራ) **ተሙኔ**
ተሙኑ ሰንት ነው። ዋጋው ሰንት ነው።
ያባት ስም ዋጋው ቢል ይገጥማል።

379. **ተማረች - ትምህርተ**
ልጆችን ማስተማር ይገባል (ዘጸ. 12፥25)።
ያባት ስም ጥበብ ቢል ይገጥማል።

380. **ተምኔት** (ግእ)
ሐሳብ፣ ምኞት ማለት ነው።
ረከብኩ ስእለትየ ረከብኩ ተምኔትየ ።
ትርጉም፤ ልመናየን ፣ ምኞቴን አገኘሁ ማለት ነው። **ተምኒት**
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

381. **ተረጬች**
እንደ ጠበል መዳረስ፤ ለኹሉ ተዳረሰች።
ያባት ስም ንጥርወርቅ ቢል ይገጥማል።

382. **ተረዳች**
መረዳት መገንዘብ ይኾናል። መታገዝ ታገዘች ይኾናል።
ያባት ስም ሃይማኖት ቢል ይገጥማል።

383. **ተረፈችልኝ - ተረፈች**
ከመከራ ወጣች ፣ ቀረች ።
ያባት ስም ለዓለም ቢል ይገጥማል።

384. **ተስማሽ - ተሰሙ**
ሰሜትን ያመለክታል ። በጆሮ መስማትን ያመለክታል።
ያባት ስም ነጻነት ቢል ይገጥማል።

385. **ተስፋ - ተስፋዓለም**
ናፍቆት (መጓጓት)፣ ምኞት፣ አለኝታ እና መተማመን የሚገኝበት። ተስፋ በዚህ ዓለም አይወሰንም (ሮሜ.15፥13 ዕብ.11፥1)።
**ተስፋይ - ተስፋዬነሽ - ተስፋነሽ**



386. **ተሻለች - ተሻይ**
በማወዳደር ከሌላው በለጠች።
ያባት ስም በምነት ቢል ይገጥማል።

387. **ተሻወርቅ** - የተፈለገች ወርቅ።

388. **ተሾመች**
ማዕርግ አገኘች ፤ ከፍ ከፍ አለች።
ያባት ስም ላውጋለት ቢል ይገጥማል።

389. **ተቀባሽ**
ቅባት ፣ ግርማ ሞገስ ፣
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።

390. **ተቋመ - ተቋም**
የብርሃን መቋሚያ መቅረዝ (ዘጸ. 40፥4)።
ያባት ስም ወርቅነኽ ቢል ይገጥማል።
**ተቋመ ወርቅ - ተቋመ ማሕቶት** (ግእ)

391. **ተናኘች - (ተናኜ) ተናኘወርቅ**
ተሰጠች ፣ ታደለች፣ ተሰራጨች፣ ተነዛች ተበተነች፣ ተዘራች፣ ተበረከተች ማለት ነው። በዚህ ስም የራስ መኰንን እናት **የዐፄ ኃይለ ሥላሴ አያት ልዕልት ተናኘወርቅ** ይባሉ ነበር። እንዲሁም **የቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ የመጀመሪያ ልጅ ልዕልት ተናኘወርቅ** ይባሉ ነበር።

392. **ተንከተም** (ግእ)
መወጣጫ (መሰላል) ማለት ነው።

393. **ተአምር (ታምር)**
አስደናቂ ድርጊት ። የማይኾነው ሲኾን። ድንቅ ነገር ከእግዚአብሔርና ከቅዱሳኑ የሰዎችን ችግር የሚያቃልል ማለት ነው። (የሐዋ. 9፥36 - 41 ፤ 20፥9 - 12)።
**ተአምርነሽ - ተአምራቴ - ተአምራትነች**
**ተአምረ ማርያም** ክርስትና ስም።

394. **ተክለች**
አታክልትን ሊኾን ይችላል።
ያባት ስም **መሠረት** ቢል ይገጥማል።

395. **ተካበች**
ተደራረበች ፤ ካብ ካብ ተደረገች ፤ ከፍ ከፍ አለች። **ተካበወርቅ - ተካቡ**
ያባት ስም **እሸቴ** ቢል ይገጥማል።

396. **ተክሊል**
ሌላ ሰው የማይደርስበት የተከለለ ። በመከለሉ ተጠበቀ ማለት ነው።
ያባት ስም **ክብሩ፣ ጸጋው** ቢል ይገጥማል

397. **ተኳላሽ**
ደመቅሽ፣ ተቀባሽ፣ ጠራሽ፣ ተወለወልሽ፣ ተዋብሽ...። **ኵል** የተኳለች ማለት ነው። ዓይንን ለማሳመር የሚቀቡት ቅባት። ሸፋሽፍት በኵል መኳኳል (2ነገሥ. 9፥30፤ ኤር. 4፥30 ፤ ራእ. 3፥18)።
ያባት ስም **ውበቴ** ቢልይገጥማል።

398. **ተወዳጅ – ተወዳድ**
በሾክ መካከል እንዳለ የሱፍ አበባ እንዲሁ ወዳጄ (ተወዳጅ) በቆንጆጅት መካከል ናት (መኃ. መኃ. 2፥2)።
ያባት ስም **አገሬ** ቢል ይገጥማል።

399. **ተዋበች – ተዋቡ**
አማረች፣ ቆነጀች ማለት ነው ።
(1ሳሙ. 17፥42) አንቺ በሴቶች ዘንድ የተዋብሽ ሆይ (መኃ. መኃ. 1፥8)።

400. **ተዘራሽወርቅ**
ተባዛች ፣ ተዳረሰች ።
**ተዘራወርቅ - ተዘሩ - ተዘራ**

490. **ነጸርት** (ግእ)
አየች ማለት ነው። ነጸረአብ
ያባት ስም ፍሬሰላም ቢል ይገጥማል።

491. **ነጻነት**
ነጻ መኾን ፣ ካገልጋይነት ፣ ከመጨቆን
ነጻ መውጣት (ገላ. 5፥1)።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

492. **ኑሪልኝ**
ቁሚልኝ ፣ ቆይልኝ፣ ማለት ነው።

493. **ኑኑሸት**
የሙገሳ ስም ፤ ከዋና ስም ቀድም ብሎ
የሚሰየም። **ኑንሽ - ኒኒ - ኒና - ናኑ**
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።
**ኑኑ - ኑኑሼ - ኑኑሽ - ኑኑዬ**

494. **ኒሻን (ሊሻን) — ኒሻነወርቅ**
በክብር፣ በሥራ ውጤት የሚሸለም።
ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።

495. **ናርዶስ**
የናርዶስ ቅጠል ፤ ደስ የሚያሰኝ ሽቱ ናር
ዶስ ወሀበ መዐዛሁ ። የኔ ናርዶስ መዐዛ
ውን ሰጠ (ማኅ. ዘሰሎ 1፥12 ፤ 3፥20 ፤
4፥13) ። ናርዶስ ዘምስለ መጽርይ ቀጺመ
ታት ወቀናንሞስ። ትርጉም ፤ ናርዶስና
ከቀጋ ጋራ ሽቶ ሣርና ቀረፋ ማለት ነው።

496. **ናፍቆት**
ጽኑ ምኞት፤ የሚወዱትን በፍቅር ማሰብ።
(2ኛ ቆሮ. 7፥7፥11፤ 1ኛ ተሰ. 2፥17፤ 3፥6)

497. **ንባበ — ነበበች - ነበቡ** (ግእ)
ነበበ ከሚለው የወጣ፦ ተናገረች ፣ ተረጎ
መች ማለት ነው።
ከውርድ ንባብ በኋላ ተማሪ እየጮኸ በፍ
ጥነት የሚናገረው የሚያነበው።
ያባት ስም ነቢያት ቢል ይገጥማል።

498. **ንብረቴ - ንብረት**
ሀብቴ፣ ገንዘቤ፣ ቅርሴ፣ ኻብት ...።
ቅርስ ሊኾን ይችላል ።
ያባት ስም ታያቸው ቢል ይገጥማል።

499. **ንቧ - ንብወርቅ - ንብነሽ**
ተወዳጅ ማርን የምትሰጥ ነች ። በኃይለኝ
ነት ትመሰላለች (መዝ. 117 (118)፥12)።
ንቦ ንቦ አትናደፊ ንቦ አትናደፊ እንዳለ
ዘፋኝ ።

500. **ንዋይነሽ** (ንዋይነሽ) - **ንዋዬ**
ሀብት ሲመጣ የምትወለድ ልጅ ወይም
ራሷ ሀብት ኾና በመምጣትዋ ንዋይነሽ
ትባላለች።

501. **ንጋቷ - ንጋት - ንጋቴ**
ማለዳ ፣ ጠዋት ...።
ገነኛዋ ባለቅኔ አቀንቃኝ ንጋቷ ከልካይ
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዷ ናቸው።

502. **ንግርቱነሽ**
ትንቢቱ ፣ ተስፋው ፍጻሜ ያገኘሽ ...።
ያባት ስም ተስፋዬ ቢል ይገጥማል።

503. **ንግሥት**
በቅዱስ መጽሐፍ የኢትዮጵያ ንግሥቶችን
ያመለክታል፤ ማክዳ (1ኛ ነገ. 10፥1 ማቴ.
12፥ 42 ፤ ሉቃስ 11፥31) እንደሁም ሕን
ደኬን (ሐዋ. ሥራ 8፥27)።
**ንግሥቲ ንግሥቴ - ንግሥትባባ -**

504. **ንጥረወርቅ**
የነጠረች ንጹሕ ወርቅ እንከን የሌለባት።



ያባት ስም ተገኘ ቢል ይገጥማል።
**ንጹወርቅ - ነጠረወርቅ - ነጠረች**

505. **ንጽሕተ - ንጽሕት**
የነጻች፣ የጸዳች ፤ ሰውነትን፣ ልብስን፣
ማጽዳት፤ ከረከሰ ነገር መንጻት። ንጹሕ
መሥዋት ማቅረብ፤ ከኀጢአት መንጻት
(ዘሌ.15፥8–11፤ መዝ.50፥7፤ ሕዝ. 36፥25)
**ንጹሐን - ንጹሕ - ንጹሰው - ንጽሕና**
**ንጹፍሬ - ንጹሕብር (ንጹብር)**

506. **ኖላዊት** (ግእ)
የበግ ፣ የሕዝብ ጠባቂ (ዮሐ.10)።
ያባት ስም ቸሩ ቢል ይገጥማል።

507. **ኖኃሚን (ዕብ.)**
ደስታዬ ማለት ነው ፤
የቤተልሔም ተወላጅ የነበረች በሞአብ
የኖረች የሩትና የእርፋ አማት ነበረች
(መጽ. ሩት 1፥20)።

## - አ -

508. **አሁጂ** (ጉራ)
እግዚአብሔር ይመልከትሽ ማለት ነው።

509. **አለሙሽ**
በሕልም ፣ በራእይ።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።

510. **አለማኹ**
አለመለምኳት፣ አበጀኋት፣ አሳመርኳት፤
እንድታድግ ተንከባከብኩ ...።
ያባት ስም መኩያ ቢል ይገጥማል።
**አለማች - አለማሽ - አለማት**

511. **አለችኝ**
ወርቅ፣ ዐልማዝ፣ እንቁ ...።
ያባት ስም የማታወርቅ ቢል ይገጥማል።

512. **አለኝታ**
የወደፊት ተስፋን ያመለክታል።
ያባት ስም መከተ ቢል ይገጥማል።

513. **አለፈች - አለፉ**
ኼደች ...።
ያባት ስም ታሪኩ ቢል ይገጥማል።

514. **አሉሽ**
ውብ፣ ባለሟያ ...።
ያባት ስም ማስረሻ ቢል ይገጥማል።

515. **አላዩ**
አልተመለከቱም ...።
ያባት ስም ዕንቁባሕርይ ቢል ይገጥማል።
**አላዩሽ - አላይ - አላየንሽ**

516. **አላውጋ**
አልናገር ዝም ልበል ...።
ያባት ስም ዝና ቢል ይገጥማል።

517. **አልማዝ**
ከማዕድናት ኹሉ ዋጋው የከበረ ጠንካራ
ዕንቁ ድንጋይ (ዘጸ.28፥18፤ ሕዝ.3፥9፤ ዘካ
.7፥12)። **አልማዙ - አልማዜ**
**አልማዝወርቅ**

518. **አልባሰወርቅ** (ግእ)
የወርቅ ልበስ ማለት ነው።
በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወሕብርት። ትር
ጉም ፤ በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋ
ፍና (መዝ. 44፥9)

519. **አልታየች**
ማንም ያያት የለም ...።
ያባት ስም ያለምሸት ቢል ይገጥማል።
**አልታየወርቅ - አልታየ**
**አልታሸወርቅ - አልታዩ**

520. **አልጣሽ**
በዚህ ስም የዐፄ ቴዎድሮስ ልጅ የዐፄ ምኒልክ የመጀመሪያ ባለቤት **አልጣሽ** ይባሉ ነበር።

521. **አመቴ - አመተ**
ልጄ አገልጋዬ ማለት ነው ።
በክርስትና **አመተ ማርያም** ቢል ይኾናል።

522. **አመነች**
መጠራጠርን አስወገደች ።
ያባት ስም **በላቸው** ቢል ይገጥማል።

523. **አመዘነች – አመዘን**
ወደ አንደኛው ወገን አደላች።
ያባት ስም **በትዛዙ** ቢል ይገጥማል።

524. **አማለደች**
ተጣልተው የነበሩትን አስታረቀች ፤ አስ ማማች ማለት ነው ።
የጐደለውን ሞልታ ፤ ከእዳ፣ ከመከራ፣ ከጣጣ፣ አዳነችኝ።
ያባት ስም ታረቀኝ ቢል ይገጥማል።

525. **አማረች - አማርን - አማሩ**
ውብ መልከ መልካም ኾነች ።
ያባት ስም ውብሸት ቢል ይገጥማል።

526. **አማን** (ግእ)
እውነት ማለት ነው ።
አማን አማን እብለከ ! ከመ ዘነአምር ንነ ግር። ትርጉም ፤ እውነት እውነት እልሀ ለሁ የምናውቀውን እንድንናገር (ዮሐ. 3፥11)።
**አማኒቱ - አማኔ - አማንነሽ**

527. **አማከለች**
ከአባቷ እና ከእናቷ መልክን በትክክል ወሰደች። ወይም ኹለተኛ ልጅ መካከል የገባች ማለት ነው ።

528. **አምለሱ**
የራስ ዐሉላ እንግዳ ቁቢ ኹለተኛ ባለቤት **አምለሱ** አርአያ ይባሉ ነበር።

529. **አምሮቴ - አምሮት**
ጓጒቼ አንቺን አገኘኹ ማለት ነው።
ውልታዬ፣ ፈቃዴ፣ (ኤር. 12፥10)።
ያባት ስም **ይብቃለ** ቢል ይገጥማል።

530. **አምሳል** (ግእ) **አምሳያ**
በምሳሌ፣ በታሪክ፣ በተረት፣ ውስጠ ወይራ ንግግር ። **አምሳለወርቅ**
**አምሳለ ወርቅ** ይገብሩ ለኪ ኰስኰሰ ዘብ ሩር። ትርጉም፤ ባለ ብር ጉብጉብ የኾነ **የወርቅ ጠልሰም** እና ደርግልሻለን (መሐ. ዘሰ. 1፥11)። **አምሳለ - አምሳለች**
**አምሳሉ - አምሳልነሽ - አምሳሏ**

531. **አምባነሽ**
ከፍታ ቦታ በርቀት የሚታይ (ጊሸን አምባ)
ያባት ስም እሸቴ ቢል ይገጥማል።
**አምባወርቅ - አምባሸት**

532. **አሞኘኹሽ**
አታለልኩሽ ...።
ያባት ስም **ፍቅሬ** ቢል ይገጥማል።
**አሞኜሼ - አሞኘኝ**



533. **አሠጋሽኝ - አሠጊ - አሠጋሽ**
አባሰብሽኝ ...።
ያባት ስም ባይከዳኝ ቢል ይገጥማል።

534. **አረገደች**
አስጨፈረች ...። **አረገዱ - አረጉ**
ያባት ስም ተዋነይ ቢል ይገጥማል።

535. **አረጋሽ - አረግሽወርቅ**
መረጋጋት፣ የልብ መርጋትን ያመለክታል
ያባት ስም **በሐርወርቅ** ቢል ይገጥማል።

536. **አርሴማ** (ግሪ)
በዲዮቅልጥያኖስ ዘመን ከደናግላን ገዳም አስወጥቶ ጋብቻ ቢሻት እንቢ በማለቷ፤ በእምነቷ ስለጸናች በሰይፍ እንድትሰየፍ የተደረገች ። ሰማዕትና ቅድስት ነች (ስንክ. መስከ. 29)።

537. **አሰለፈች**
ከበስተኋላዋ በተራ አስከተለች ፤ ሥርዓ ትን አስያዘች።
ያባት ስም ሚሊዮን ቢል ይገጥማል።
**አሰለፉ - አሰለፍ - አሰለፌ**

538. **አሰማሽ - አሰማች**
ድምጽን ፣ የምሥራችን ፣
ያባት ስም ብሥራት ቢል ይገጥማል።
**አሰማሽው - አሰሜ - አሰም**

539. **አሰገደች**
ታዘዙላት ፣ አከበሯት፣ እጅመንሻ አቀረ ቡላት ።
ያባት ስም በኀይሉ ቢል ይገጥማል።
**አሰገዱ - አሰገድሻቸው**

540. **አሰፋሽ**
ቦታን ፣ ግዛትን ፣ ዝምድናን።
ያባት ስም ኀብረት ቢል ይገጥማል።
**አሰፉ - አሰፍዬ**

541. **አሳመነች**
አስረዳች፣ አወን አሰኘች፤ ስሕተትን፤ እውነትን እንዲቀበሉ አደረገች ።
ያባት ስም **መርዓዊ** ቢል ይገጥማል።
**አሳመነሽ - አሳመነችው - አሳምና**

542. **አሳበች**
አገናኘች፣ አያያዘች፣ አመጣች ማለት ነው።

543. **አሳየች - አሳየሽው - አሳዬ**
በርቀት ያለውን ፤ አስተዋወቀች።
ያባት ስም ሲሳይ ቢል ይገጥማል።

544. **አስማረች**
ይቅር አሰባለች ፤ አማለደች።
ያባት ስም በጸሎቱ ቢል ይገጥማል።
**አስማሩ - አስምሪ - አስመረት**
**አስማረወርቅ - አስምራት**

545. **አስናት** (ግብ)
የኔ ሀብት ወይም በአባቷ ወገን የኾነች ማለት ነው ። በቅዱስ መጽሐፍ ዮሴፍ የፈርኦንን ሕልም ከተረጐመ በኋላ የጶጥፋራ ልጅ አስናት ተሰጠችው ። ከሷም ምናሴንና ኤፍሬምን ወለደ (ዘፍ.41)።

546. **አስረሳሽ**
ያለፈን ነገር እንዳይታወስ አደረግሽ።
ያባት ስም ያይኔንብርሃን ቢል ይገጥማል።
**አስረሳሽኝ - አስረሳች - አስረስሽ**

547. **አስራደች**
ርዕደ ከሚለው ግስ የወጣ ነው ። ተንቀ
ጠቀጠ ፈራ ። አስራደች አንቀጠቀጠች
አስፈራች ። ግርማ ያላት ማለት ነው።
ያባት ስም ይርጋወሰን ቢል ይገጥማል።

548. **አስተካከለኝ – አስተካከለሽ**
እኩል አረገኝ ። **አስተካከለችኝ**
ያባት ስም የሺጥላ ቢል ይገጥማል።

549. **አስታረቀችኝ**
በጠብ መካከል ሰላም አወረደች። የሚያ
ስታርቁም ብፁዐን ተብለዋል (ማቴ. 5፥9፤
ፊል. 4፥2 )።

550. **አስታወሰችኝ – አስታወሳት**
የተዘነጋውን ፣ የተረሳውን።
ያባት ስም ወሮታው ቢል ይገጥማል።

551. **አስቴር**
በፋርስ ቋንቋ ኮከብ ማለት ነው ። ቆንጆ
ነበረች ወላጆቿ በልጅነቷ ዐርፈውባት የአ
ጎቷ ልጅ አሳደጋት ። የመጀመሪያ ስሟ
ሐደሳ ይባል ነበር (መጽ. አስ. 2፥7)።

552. **አስቻለች**
አስታገሠች ፤
ያባት ስም **እንዳይከፋኝ** ቢል ይገጥማል።
**አስቻሉ - አስቻሌ- አስችላ**

553. **አስናቀች – አስናቁ**
የበለጠ ኾነች። የሚተካከላት የለም።
ያባት ስም **ለዓለም** ቢል ይገጥማል።

554. **አስካል** (ግእ) **አስካለ - አስካሉ**
የወይን ፍሬ ዘለላ ማለት ነው። ደመ
አስካል እንደ ማሽላ ራስ ያለው ።
(ዘፍ. 40፥10 ፤ ኢሳ. 5፥2) **አስካለ ወይን**
የወይን ዘለላ ማለት ነው።
**አስካለ ማርያም** ክርስትና ስም።

555. **አስደሳች**
የምታምር ፤ የምትማርክ ።
ያባት ስም ፍሬገነት ቢል ይገጥማል።

556. **አስደነቀች – አስደነቅ**
በችሎታዋ ፣ ተአምር በማድረጓ።
ያባት ስም ዓለም ቢል ይገጥማል።

557. **አስጋረደች** አስጋረዱ -አስጋርጂው
ከመከራ፣ ከፈተና፤ እንዳይታይ አረገች።
ያባት ስም ሕይወት ቢል ይገጥማል።

558. **አሸነፈች**
ረታች ፤ ታግላ ፣ ተከራክራ ...።
ያባት ስም ኀብረት ቢል ይገጥማል።

559. **አሻገረች - አሻጋሪነሽ -አሻግሪው**
አሳለፈች ፤ መከራውን፣ ፈተናውን ...።
ያባት ስም ባሕሩ ቢል ይገጥማል።

560. **አቅሌስያ** (ግሪ) (**አቅሌሳ**)
የጻድቁ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እናት
አቅሌስያ ይባላሉ። ቤተ ክርስቲያን ስላሳ
ደገቻቸው እናቴ አቅሌስያ ናት ፤ አባቴ
ስምዖን (ጴጥሮስ) ነው አሉ። ገድላቸው።

561. **አበረደች**
የሚያቃጥለውን ፤ በኃይል የመጣውን
**አቀዘቀዘች**።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።

562. **አበራሽ**
ጨለማን አራቅሽ፣ አሳየሽ ...።
ያባት ስም ኮከቡ ቢል ይገጥማል።
**አበሩ - አበራች - አበር - አበርዬ**



563. **አበበች**
በዚህ ስም በኢትዮጵያ ውስጥ እጓለማው
ታን በማቋቋም የዕርዳታ ድርጅት የመ
ሠረቱ ወይዘሮ አበበች ጎበና በመባል ይታወ
ቃሉ። **አበብዬ - አበቤ - አበብ**
**አበባነሽ - አበባሽ - አበቡ - አበባ**
**አበባወርቅ - አበባየኹ - አበባዬ**
**አበባዬነሽ - አበባይ - አበባይቱ**

564. **አበዛሽ**
ብዙ አደረግሽ ...።
ያባት ስም ተድላ ቢል ይገጥማል።
**አበዜ - አበዝ - አበዙ**

565. **አበጀሽ - አበጁ**
ደግ አደረግሽ ፤ ኹለተኛው ሠራሽ ...።
ያባት ስም ጉልላት ቢል ይገጥማል።

566. **አብሠራ** (ግእ)
እንደ አበሠራት፤ የምሥራች አላት፤
ያባት ስም መላኩ ቢል ይገጥማል።

567. **አቦነሽ - አቦወርቅ - አቦዬነሽ**
የአቡየ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ነሽ ፤
ወይም አባት ነሽ ...።
ያባት ስም ተካበ ቢል ይገጥማል።

568. **አቦገረድ** (ጉራ)
በጣም ጎበዝ ማለት ነው።

569. **አቢጋኤል**
ትርጉሙ አባት ደስ አለው ማለት ነው።
የንጉሥ ዳዊት ታናሽ እኅት ። እንዲ
ሁም ሌላዋ ሚስቱ የነበረች ነች።
(1ኛሳሙ. 16፥10 ፤ 1ኛሳሙ. 25፥24)።

570. **አብረኸት** (ትግ.)
አበራች ማለት ነው።

571. **አተረፈች - አተረፉ**
ከዋናዋ ሌላ አገኘች ማለት ነው።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

572. **አታክልት**
ያባት ስም በቀለ ቢል ይገጥማል።
**አታክልቴ - አታክልቲ (ትግ)**
**አታክልትይ**

573. **አትናስያ** (ግሪ)
ከቁስጥንጥንያ ቤተ መንግሥት ልጅ
የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅድስት አት
ናስያ ትባል ነበር። የመታሰቢያ ቀኗ የሚ
ከበርላት መስከረም 10 ነው (ስን. ገጽ51
ቁ.24 ፤ ጥር 26 ገጽ684 ቁ. 26)።

574. **አትጠገብ**
በዚህ ስም የሚታወቁት የዐፄ ቴዎድሮስ
እናት እሜይቴ አትጠገብ ወንድበወሰን
ይባሉ ነበር።

575. **አትደፈር**
ማንም የማይነካት ፣ የማይጠጋት።
ያባት ስም ክብሩ ቢል ይገጥማል።

576. **አቻምየለሽ - አቻሜ**
የሚተካከልሽ የለም ማለት ነው።
ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከወይዘሮ ማረፊያ
የወለዷቸው አቻምየለሽ ይባሉ ነበር ።

577. **አነስተስያ** (ግሪ)
ትንሣኤ ማለት ነው፤

ሴ

በትንሣኤ ጊዜ የሚወለዱ ይህ ስም ይሰየ
ምላቸው ነበር ። በመጀመሪያው በሰማዕ
ታት ዘመን በጣም ይታወቅ ነው።

578. **አንቀጸ** (ግእ)
መውጫ ማለት ነው።
ያባት ስም ብርሃን ቢል ይገጥማል።
**አንቀጸሰላም - አንቀጸአድኅኖ**
**አንቀጸ ብርሃን**

579. **አንቺነሽ**
ተስፋ፣ አለኝታ። በሆድ አንቺ ነበርሽ?
ያባት ስም ሰይፉ ቢል ይገጥማል።
**አንቻለም - አንቺዬ - አንችናየሁ**
**አንቺእናኔ - አንቺኹኝ**

580. **አንዳርጊያቸው**
አስማሚያቸው፣ አስታርቂያቸው ...።
ያባት ስም ይርጉ ቢል ይገጥማል።

581. **አንቺናሉ (አንቺንአሉ)**
አንቺን ፈለጉ ...።
ያባት ስም ደሳለኝ ቢል ይገጥማል።

582. **አንቺንሰጠኝ**
ልዩ ውብ ሰጠኝ ጌታ ...።
ያባት ስም ታሪክ ቢል ይገጥማል።

583. **አንጓችነሽ — አንጓች**
ወዳጄነሽ ለማለት ። እንጎቻ የምታነጉቺ ...።
ያባት ስም ጥጋቤ ቢል ይገጥማል።

584. **አካሌ**
የኔ አካል ማለት ነው።
ያባት ስም ብርሃን ቢል ይገጥማል።
**አካልነሽ - አካል - አካለ**
አካለ ሥላሴ ክርስትና ስምን ተመልከቱ።

585. **አክሊለ**
ዘውድ የራስ ጌጥ ሽልማት፤ የክብር ምል
ክትና ትልቅ ማዕረግ ያላቸው ሰዎች የሚ
ቀዳጁት። (2ጢሞ. 4፥8 ፤ ራእ. 2፥10 ፤
ማር. 15፥17 ፤ ሰቆ. 5፥16)።
ያባት ስም ጽጌ ቢል ይገጥማል።
**አክሊለወርቅ - አክሊል - አክሊሏ**
**አክሊልሰጠኝ**
አክሊለ ጊዮርጊስ ክርስትና ስም ተመልከች።

586. **አወጣሽ - አወጡ**
ከችግር ፣ ከመከራ ፤ አሻገርሽ ።
ያባት ስም መልአኩ ቢል ይገጥማል።

587. **አዋየኹሽ**
ያባት ስም ተስፋ ቢል ይገጥማል።

588. **አዘነጋሽ — አዘነጋች**
ዘንግዐ ከሚለው ይወጣል፤ አስረሳሽ ...።
ያባት ስም ተድላ ቢል ይገጥማል።

589. **አዛለች - አዛሉ**
አደከመች ፣
ያባት ስም ዘማቹ ቢል ይገጥማል።

590. **አዜብ**
የደቡብ ምዕራብ ያለ አቅጣጫ ፤ ንገ
ሥት ሳባ (ማክዳ) የነገሠችበት ያገር ስም
ስመ መንግሥቷ ነው።
(ማቴ. 12፥42 ፤ ዘፍ. 12፥9 ፤ 13፥1)።

591. **አዝመራዬ**
እርሻዬ፣ አጨዳዬ፣ ቁፋሮዬ ፣ የመከር
ፍሬዬ ...። ወንጌልም አዝመራ ነው።
ያባት ስም በዛብህ ቢል ይገጥማል።
**አዝመራይቱ - አዝመራ - አዝመረት**



592. **አዝማች - አዝማችነሽ**
ፊት መሪ ፣ ፊታውራሪ ነሽ።
ያባት ስም አሉባለው ቢል ይገጥማል።

593. **አዝፋረወርቅ** (ግእ)
የወርቅ መጐናጸፊያ ማለት ነው።
(መዝ. 44(45) ፥ 13)

594. **አየኹ**
ተመለከትኩ ፣ አረጋገጥኩ ...።
ያባት ስም ጸጋ ቢል ይገጥማል።
**አየኹብርሃን - አየኹሽ - አየኹብዙ**
**አየኹዓለም - አየኹጸጋ - አየኹልሽ**
**አይቼሽ - አየልዩ - አየሽ - አየኋት**

595. **አየናቸው - አየናት**
ተመለከትናቸው ...።
ያባት ስም ተዋሕዶ ቢል ይገጥማል።

596. **አያኽሉሽም**
አይተካከሉሽም በውበት በቁንጅና ...።
ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከወይዘሮ ማለፊያ
ከወለዷቸው ልጆች አንዷ ልዕልት አያ
ህሉሽም ይባሉ ነበር ።
**አያኽሉሺ - አያከሉሽ - አይችሉሽም**

597. **አያልነሽ**
ኃያልነሽ ቢል ግእዝ ነው። ኀይልን ያመ
ለክታል ።
ያባት ስም መድኀኒት ቢል ይገጥማል።

598. **አያንቱ** (ኦሮ)
በድሏ ፣ ዕድለኛ ማለት ነው።

599. **አይድዐ** (ግእ)
አስተማረች፣ አመለከተች፣ ተናገረች አሳ
ወቀች ማለት ነው።
ወአነ አየድዕ ግብርየ ለንጉሥ።
ትርጉም ፤ እኔ ሥራዬን ለንጉሥ እናገራ
ለሁ (መዝ. 44 ፤ ምሳ. 8፥6 ፤ አስቴ. 2፥2
0)። ዓይድአ ተመልከች።

600. **አደላሽ**
ወደ አንድ ወገን ኾንሽ።
ያባት ስም በኀይሉ ቢል ይገጥማል።

601. **አደመች** (ግእ)
አማረች ቆነጀች ማለት ነው።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።

602. **አደራዬ**
አደራ በሰማይ አደራ በምድር እንደሚባ
ለው ...። አለብኝ አደራ ...።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።

603. **አደነቁ — አደነቅሽ - አደነቀች**
ደምግባቷን ፣ ውበቷን አይተው ...።
ያባት ስም ደሳለኝ ቢል ይገጥማል።

604. **አደይ — አደይ አበባ**
በመስከረም የሚወጣ የመጸው አበባ
ቀለሙ ቢጫ የኾነ ደስ የምትል ማለት
ነው።

605. **አዱኛሽ** (ኦሮ. ግእ)
አደነ ከሚለው የወጣ ነው።
ሀብትሽ ማለት ነው።
ያባት ስም በዛ ቢል ይገጥማል።

606. **አዳምነሽ**
የሰው ዘር ለማለት የሚሰየም ነው።
ያባት ስም ዘሩ ቢል ይገጥማል።
**አዳምወርቅ - አዳሚ**

ሴ

607. **አዳነችኝ**
ከህልፈት ፣ ከመጥፎ ነገር ሰወረች ...።
ያባት ስም በእምላኩ ቢል ይገጥማል።
**አዳነች - አድኒ - አዳኜ - አድኅነ**

608. **አድማሰወርቅ – አድማስ**
አጥናፈ ወርቅ ማለት ነው።
ሰማይና ምድር የተገናኙ የሚመስልበት ቦታ ወይም የምሥራቅ ጫፍ በትፈነጥቅ የሚታየው ወጋገን ማለት ነው።

609. **አጂየት** (ጉራ)
እመቤት ማለት ነው።

610. **አገሬ - አገርነሽ**
የትውልድ ቦታ፤ እርስት ።
ያባት ስም አማረ ቢል ይገጥማል።
**አገርዓለም - አገር - አገሬነሽ**

611. **አገኘኹሽ – አገኘኹ**
ሴት ልጅ ወለድኩ ማለት ነው።
ያባት ስም ፍቅሬስም ቢል ይገጥማል።

612. **አጊኔ** (ዶር) ደመቀች ማለት ነው።

613. **አጋረደች**
ከመከራ ከችግር ከለለች ሰወረች ማለት ነው።

614. **አጎዜ** (ዶር) ገንፎ ማለት ነው።

615. **አጓጓሽ – አጓጓሽኝ**
የደስ ደስ ያለሽ ...።
ያባት ስም ውብእሸት ቢል ይገጥማል።

616. **አጥሊ – አጥሌ**
መከራን አሳልፊ፣ ጋርጂ ፤ ጥላሽን፣ ድባብሽን አጥሊባቸው ...።
ያባት ስም የራስወርቅ ቢል ይገጥማል።

617. **አጥናፍ (አጽናፍ ግእ)**
ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ፍጻሜ የሌለው ማለት ነው፤ ለግዛትም ይኾናል።
**አጥናፏ (አጽናፋዊ) - አጥናፈዓለም አጥናፈወርቅ**

618. **አፀደ - አፀዱ** (ግእ)
የአትክልት የመዝናኛ ቦታ ጓሮ ፤ አጨደ ማለት ነው።

619. **ኢትዮጵያ**
ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሐ ሐበ እግዚአብሔር፤ ትርጉም፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ተዘረጋለች (መዝ. 67 (68)፥31)። በሴት አንቀጽ መጠራቷ ፍቅርን ያመለክታል።

620. **ኢየሩሳሌም**
ቅድስት አገር ...።
ያባት ስም ገዳሙ ቢል ይገጥማል።

621. **ኤልሳቤጥ (ዕብ) – ኤልሳ**
በቅዱስ መጽሐፍ በመጀመሪያ የካህኑ የአሮን ሚስት (ዘጸ. 6፥23) ፤ በአዲስ ኪዳን የካህኑ የዘካርያስ ሚስት እና የዮሐንስን መጥመቁ እናት ። ፀንሳ ሳለች ቅድስት ድንግል ማርያም በጎበኘቻት ጊዜ ፅንሱ በማሕፀኗ ዘለለ (ሉቃ. 1፥39)። በዚህ ስም ብዙ ኢትዮጵያውያን ይጠሩበታል።

622. **ኤደና (ዕብ)**
ደስታ ማለት ነው። የአቡነ አረጋዊ እናት በዚህ ስም ይታወቃሉ ።



623. **ኤዶም** (ዕብ)
ቀይ ማለት ነው ።
ኤሳው የተሰየመበት ስም ነው ። እንዲሁ የአገር ስም ነው (ማር. 3፥8) በዚህ ስም ወንዶችም ሴቶችም ይጠሩበታል።

624. **ኤፍራታ** (ዕብ)
ፍሬያማ ቦታ ማለት ነው።
ራሔል የተቀበረችበት ቦታ። በኋላ ዘመን የዳዊት ከተማ የኾነችው ጌታ የተወለደባት ቦታ ቤተልሔም ነች። ናሁ ሰማዕናሁ በኤፍራታ ። ትርጉም፤ እነሆ በኤፍራታ ሰማነው (መዝ. 131(132)፥6)።

625. **እሌኒ** (ግሪ)
የምታበራዋ ብርሃን ማለት ነው ።
የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ፤ ኢየሩሳሌም ኼዳ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መስቀል አስቆፍራ ያስወጣች ፤ አብያተ ክርስቲያንን ያሳነጸች ነች። በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመደ ስም ነው። የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ (ቆስጠንጢኖስ) ሦስተኛና የመጨረሻ ባለቤት እሌኒ ይባላሉ።
ገጽ 127 : 57 ይመልከቱ

626. **እልፍነሽ** (ግእ)
ብዙነሽ ለማለት ነው (ዐሥር ሺህ)።
በዚህ ስም በማራቶን ሩጫ ወርቅ በማስገኘት አገሯን ያስጠራች ኢትዮጵያዊት እልፍነሽ ዓለሙ ነች። **እልፍያምጡ**
**እልፍዓለም - እልፌ - እልፍኝ**
**እልፍአደግ - እልፍዋጋሽ - እልፏ**

627. **እመቤት**
ባለቤት፣ የተከበረች የደስ ደስ ያላት።
በቤተሰብ መካከል አስተዳዳሪ፣
ኀላፊና ተወዳጅ የኾነች ማለት ነው።
(2ኛ ዮሐ. 1፥2)። **እሙሼ - እማዬነሽ**
**እመቡ - እሙሰላም - እመናት**

628. **እማዋይሽ**
የምነግርሽ አለኝ ማለት ነው ።
ያባት ስም ዘገየ ቢል ይገጥማል።

629. **እምሯ**
አሻራዋ፣ ምልክቷ፣ ቁንጮዋ፣ ጫፏ ፣ አሻራዋ፣ ዓይኗ ... ማለት ነው።

630. **እምቅድመ-ዓለም** (ግእ)
ከዓለም በፊት።
ያባት ስም ታምሩ ቢል ይገጥማል።

631. **እምዩ**
እናት ነሽ ለማለት በእናትነት ቦታ የሚሰጥ ስም ነው።
**እምየነሽ - እምዬ - እመይቱ እማዩ**

632. **እምነት – እምነቴ**
በአምላክ ወይም በሰው ፍጹም ተስፋ ማድረግ። ሰው በእምነት ሲኖር በእግዚአብሔር ቃል ይመራል። በተስፋ ይኖራል (ሮሜ. 4፥16 – 22 ፤ ዕብ. 11)።
ያባት ስም ይልቃል ቢል ይገጥማል።

633. **እምወድሽ (ምወድሽ)**
መውደድን ያመለክታል።
ያባት ስም ፍሬሰላም ቢል ይገጥማል።

634. **እሰይነሽ – እሰዬ**
ልጅ አገኘሁ ደስታ ነሽ፤ ይኹንልኝ።
ያባት ስም ፍቅሬ ቢል ይገጥማል።

635. **እስከላለም - እስካለም**
እስከ መጨረሻው ...።
ያባት ስም ፍጹም ቢል ይገጥማል።

ሴ

661. **ከበቡሽ - ከበበች - ከበበሽ**
ብዙዎች ፤ ዙሪያውን ከበቡ።
ያባት ስም ዓለሙ ቢል ይገጥማል።
**ከበበፀሐይ - ከበቡ - ከበቧት**

662. **ከበደች**
ከበረች ማለት ነው በቁጥር በሚዛን
በዚህ ስም ከሚታወቁት አንዷ የራስ
ሥዩም መንገሻ ሴት ልጅ የደጃዝማች
አበራ ካሣ ባለቤት በማይጨው ጦር ሜዳ
ዐርበኛ የነበሩት ከበደች ሥዩም ይጠሩበ
ታል (1904 - 1976 ዓ.ም.)። **ከበድሻቸው**

663. **ኩብኩብ** (ግእ)
ሰርግ ማለት ነው።
ከብከበ ኮነ በቃና ዘገሊላ ። ትርጉም ፤
በገሊላ ክፍል በቃና ሰርግ ኾነ (ዮሐ. 2፥1)
ያባት ስም መርዓዊ ቢል ይገጥማል።

664. **ከተማነሽ - ከተማ - ከተማሽ**
የደመቀች የሰለጠነች ...።
ያባት ስም ይድነቃቸው ቢል ይገጥማል።

665. **ከፍያለች – ከፍአለች**
ወደላይ የታየች ። በቁመት ፣ በሙያ ፣
በውበት፣ **ከፍነሽ - ከፍከፍ**
ያባት ስም ጉልላቴ ቢል ይገጥማል።

666. **ኰሉብርሃን** (ግእ)
ኹሉብርሃን ማለት ነው ።
ያባት ስም ታየ ቢል ይገጥማል።

667. **ኮሊቱ - ኮሊ** (ኦሮ)
ኩል የተኳለች ማለት ነው። ዓይንን ለማ
ሳመር የሚቀቡት ቅባት ።የጥንት ሰዎችም
ዘመናዊዎችም የዓይናቸውን ሽፋሽፍት
በኩል ይኳዋሉ ነበር (2ነገ. 9 ፥ 30 ፤
ኤር. 4 ፥ 30 ፤ ራእ. 3፥18)።

668. **ኰሬ – ኰሬባቸው**
ተንቀባረረባቸው ...።
ያባት ስም ሙሉዓለም ቢል ይገጥማል።

669. **ኪሮስ** (ግሪ)
በዚህ ስም እመቤታችን ቅድስት ድንግል
ማርያም በሥዕሏ ተገልጸ ያነጋገረችው
ጸሎተኛ መነኩስ አባ ኪሮስ በመባል የሚ
ታወቁ ጻድቅ ናቸው (ስን. ሐም.8 ገጽ.535-
-541) ። ወለተ ኪሮስ ከሚለው የክርስትና
ስም ተወስዶ ኪሮስ በማለት ይጠራሉ።

670. **ኪያ** (ኦሮ) የእኔ ማለት ነው።

671. **ኪያኪ** (ግእ) **ኪያኪሠናይቶ**
አንቺ በጎ መልካም ማለት ነው።

672. **ኪዳኗ** (ግእ)
የተዋዋለችው ቃሏ ...።
ተካየደ ካለው የወጣ ነው። ተዋዋለ፣ ቃል
ኪዳን ተጋባ፣ ተማማለ ማለት ነው።
(ዘዳ. 29፥1 ፤ ኤር. 31፥31 ፤ 32፥33)።

673. **ካሰች**
ዋጋ ከፈለች ፤ ከፈለችኝ።
ያባት ስም ሰሙኝ ቢል ይገጥማል።
**ካሳነሽ - ካሰችኝ - ካሰኝ - ካሱ
ካሕሢት - ካሕሣይ - ካሣይቱ
ካሣይነሽ** (ትግ)

674. **ካንቺወዲያ**
ሌላ አያስፈልገኝም ፤ ፍጹምነትን ያመለ
ከታል።
ያባት ስም መዐርጉ ቢል ይገጥማል።

675. **ኬና** (ኦሮ) ስጦታ ማለት ነው።



676. **ክልልተወርቅ – ክልነሽ**
ከለለ ከሚለው ግስ ፤ ጋረደ አከበረ ይመ
ጣለ ። የተከበረች ወርቅ።
ያባት ስም መንግሥቴ ቢል ይገጥማል።

677. **ክብር**
ከፍተኛነትን፣ ብርሃንነትን ፣ ሰው በንጽሕ
ናው ክብር ያገኛል (ሮሜ. 13፥7)።
ያባት ስም ማኅተቤ ቢል ይገጥማል።
**ክብሬነሽ - ክብረወርቅ - ክብሯ
ክብረመንግሥት - ክብርነሽ - ክብሩ
ክብረዓለም - ክብርዬ - ክብረማርያም
ክብረ ቅዱሳን** ክርስትና ስም።

678. **ክበበ**
ዙሪያዋ የተከበበ ፤ የተሾመች።
ያባት ስም ጌራወርቅ ቢል ይገጥማል።
**ክበቢያቸው - ክበቧ - ክበበፀሐይ
ክበብነሽ - ክብነሽ - ክቢቱ
ክበበወርቅ - ክብዬ - ክቤ**

679. **ክባሰወርቅ**
ከበሰ ከሚለው ግስ ፤ ጠመጠመ ጠጉር
ጠቀለለ ማለት ነው።

680. **ክትነሽ**
የተከተተች ፤ በዐዲስነት ያለች።
ያባት ስም ደባለኝ ቢል ይገጥማል።

681. **ክፈይ**
እንደ ድርሻቸው አዳርሽ፤ እኩል እኩል
አካፍይ ፤ ሚዛን ኹኝ ...።
በዚህ ስም የሚታወቁት የቴጌ ጣይቱ
ታናሽ ወንድም የራስ ወሌ ብጡል ሴት
ልጅ ወይዘሮ ክፈይ ወሌ ይባላሉ። የዐፄ
ዮሐንስ ልጅ የራስ መንገሻ ባለቤት።

682. **ኰራሽ - ኰራን - ኰሬ**
ኩራት ማለት መቆነን፣ መኮፈስ ነው።
ኩራት ልጅ በመገኘቱ።
ያባት ስም በቃሉ ቢል ይገጥማል።

683. **ኮከቤ - ኮከብ - ኮከብነሽ**
ኮከቦች የአምላክን ክብርና ታላቅነት
ያበታውቃሉ (ዘፍ.1፥16 ፤ አሞ. 5፥8)።

## - ኸ -

684. **ኹለመናሽ - ኩለመናሽ** (ግእ)
ፍጹም አካል እና ሙሉ አካል
(ሉቃ. 11፥34)።
ውበትን ለመግለጽ ይሰየማል።
ያባት ስም አሸናፊ ቢል ይገጥማል።
**ኹሉዬ - ኹሉምታየ - ኹሉምይፈር
ኹሉምሰው - ኹሉባንቺ - ኹሉታዬ
ኹሉንቻይ - ኹሉንዓየሁ -ኹሉዓለም
ኹሉዐዲስ - ኹሉአገሬ - ኹሉአገር
ኹሉአገርሽ - ኹሉወርቅ -ኹሉይማር
ኹሉግርጌሽ - ኹሉዋ - ኹልጊዜ
ኹሉሰፍራሽ**

685. **ኻብታም** (አማ)
ከበተ፣ ተካበተ ካለው ካብታም (ግእ)
**ኻብታሟ - ኻብትይ - ኻብቴዋ
ኻብቴነሽ - ኻብታለም - ኻብትሽ
ኻበትአገኘሁ - ኻብትሽይመር
ኻብትሽደግ - ኻብትሽወርቅ**
ሀብት የሚለውን ተመልከች።

686. **ኾነችልኝ**
ኮነ ከሚለው ግስ ፤ ኾነ ይወጣል ። ያሰ
ብኩት ኾነ ።
ያባት ስም ዐልማዝ ቢል ይገጥማል።

ለሃይማኖት መሪዎችና ለመንግሥት የሚ ሰጥ (ዘፍ. 14፥20)።
ያባት ስም ሰጠኝ ቢል ይገጥማል።
**ዐሥራተ ሥላሴ** ክርስትና ስም።

713.**ዐረፋዐይኔ**
ከመጓጓት ፤ የዓይን ማረፊያ ።
ያባት ስም ተመስገን ቢል ይገጥማል።
**ዐረፈሽዋ - ዐረፋች**

714.**ዐሰበልኝ** (ሐሰበ (ግእ))
ተቆረቆረልኝ፣ ተጨነቀልኝ ...።
ያባት ስም ወዳጁ ቢል ይገጥማል።
**ዐሰበች - ዐሰበችወርቅ**

715.**ዐሳቤ** (ሐሳቤ (ግእ))
ተፈጸመ፣ ተቃና፣ ኾነልኝ ...።
ያባት ስም ፍጹም ቢል ይገጥማል።
**ዐሳቢ - ዐሳብ - ዐሳብነሽ**

716.**ዐበረች**
ተባበረች፣ ዐብራ ኾነች ...።
ያባት ስም በኀብረት ቢል ይገጥማል።

717.**ዐወቀች**
ተረዳች ...።
ያባት ስም መሸሻ ቢል ይገጥማል።

718.**ዐዘነች**
ያባት ስም ዘማርያም ቢል ይገጥማል።
**ዐዛኜ - ዐዛኝቱ - ዐዘነች - ዐዘነችልኝ**

719.**ዐየለች** (ኀየለች (ግእ))
በዚህ ስም የምትጠራው በሩጫ ውድ ድር አገሯን ለዓለም ያሳወቀች ዐየ ለች ወርቁ ነች። **ዐየሉ - ዐያልነሽ**

720.**ዐይናለም** (ዐይንዓለም)
ማስተዋልን፣ ብርሃንን ማየትን እንዲሁም የሰውን ጠባይንና ስሜት ይገልጣል (ዘዳ. 7፥16 ፤ ኢሳ. 5፥15 ፤ ሕዝ. 14፥16)።
ያባት ስም ብርሃኔ ቢል ይገጥማል።
**ዐይናበባ - ዐይናቸው - ዐይናዲስ**
**ዐይንሽት - ዐይኔነሽ - ዐይኔ**
**ዐይነፀሐይ - ዐይኒዬ - ዐይንዋጋ**
**ዐይናማ - ዐይኔ**

721.**ዐደሰች** (ሐደሰች (ግእ))
ዐዲስ አደረገች ...።
ያባት ስም ሕይወት ቢል ይገጥማል።
**ዐዲሴ - ዐዲስ - ዐዲሷ - ዐደሱ**
**ዐደሰወርቅ**

722.**ዐዲስዘመን** (ሐዲስ (ግእ))
ዐውደ ዓመት ፤ ክረምት አለፈ።
ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የጣሊያን ጦርነት እንዳ በቃ ከድል በኋላ ጋዜጣዋን ዐዲስ ዘመን አሏት ። **ዐዲስ ምራፍ**
ያባት ስም ዮሐንስ ቢል ይገጥማል
**ዐዲስ - ዐዲሳለም - ዐዲስ ሕይወት**

723.**ዐጀቡሽ — ዐጀብነሽ**
ያባት ስም ሙሉዓለም ቢል ይገጥማል።

724.**ዐጤነሽ** (አጤነሽ (ግእ))
ያባት ስም መንግሥቴ ቢል ይገጥማል።

725.**ዐጸደ ወይን** (ግእ) (**አጠደ ወይን**)
ስፍራ ቦታ፣ የቤተ ክርስቲያን ዛፍ፣ አድባር ። የወይን አታክልት ።
ዐጸደ ወይን አፍለስከ እምግብጽ።
ትርጉም፤ ከግብጽ የወይን ግንድ አመጣኽ (መዝ. 79(80)፥8)። አጠደ ዐማርኛ ነው።
**ዐጸደ - ዐጸዱ = አፀደ** ተመልከት።



726.**ዓለም - ዓለምዘውድ**
ዓለም ያለነበረበት ጊዜ ነበር በኋላ ግን እግዚአብሔር አስገኘው ። ጠቅላላ ፍጥረ ትን የዓለምን ሕዝብ ማለት ይኾናል ። (ዮሐ.1፥10 ፤ 16፥21)
**ዓለመወርቅ - ዓለመብርሃን**
**ዓለምሽዋ - ዓለሚ - ዓለሜ - ዓለም**
**ዓለምሰፉ - ዓለምሸት - ዓለሚቱ**
**ዓለምቀናሽ - ዓለምኛ - ዓለምቀረ**
**ዓለምባንቺ - ዓለምብርሃኔ**
**ዓለምብርሃን - ዓለምተሰፉ**
**ዓለምታሪክ - ዓለምታየ - ዓለምላንቺ**
**ዓለምሰላም - ዓለምትኹን - ዓለምነሽ**
**ዓለምይርጋ - ዓለምናት - ዓለምዬ**
**ዓለምይሰፉ - ዓለምገላ - ዓለምገነት**
**ዓለምፀሐይ - ዓለምጸጋ - ዓለምፍሬ**

727.**ዓላማዬ**
ለዘመቻ ለሌላም የሚይዙት ምልክት ወይም የሚያቆሙት ምልክት (ዘኍ. 2፥2 መሐ. 6፥4 ፤ የሐዋ. 28፥11)።

728.**ዓባይ**
ትልቅ ማለት ነው። በዚህ የሚጠራው ትልቁ ወንዝ ጊዮን ነው (ዘፍ. 2፥13)።
**ዓባይሽ - ዓባይነሽ - ዓባይነች**

729.**ዓያና** (ኦሮ.)
በዓል፣ ሰንበት እንዲሁም ቀናኝ፣ ቆንጆ ማለት ነው። **ዓያንቱ - ዓዬቱ**

730.**ዓይዳ** (ዐረ) **ዓይድዐ**
ምኞት ማለት ነው።

731.**ዔደን** (ዕብ) **ዔዶም** (ግእ)
ምቹ ሥፍራ፣ ገነት ተድላ የግእዝ መጽ ሐፍ ዔዶም ይላል። የሰላም የደስታ ቦታ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ፈጥሮ ያስ ቀመጠበት ቦታ ከስሕተት በፊት የነበሩበት ምድረ ገነት (ዘፍ. 2፥10፤ 3፥24፤ ዘፍ.1፥8)

732.**ዕርቀሰላም** (**ርቀሰላም**)
ጠብ ባለባቸው ኹለት ሰዎች መካከል ሰላም ሲኾን ዕርቅ ይባላል። ከፈጣሪ ጋር መታረቅ ፤ የሚያስታርቁም ብፁዐን ተብለ ዋል። (ማቴ. 5፥9 ፤ ፊል. 4፥2 )።
ያባት ስም ወረደ ቢል ይገጥማል።
**ዕርቀኢየሱስ - ዕርቅነሽ - ዕርቁ**
**ዕርቃለም**

733.**ዕሴተ** (ግእ)
ዋጋ ማለት ነው።
ዕሴተ ፍሬሀ ለከርሥ ። ትርጉም ፤ የሆድም ፍሬ የሱ ዋጋ ነው (መዝ.126፥3)።

734.**ዕንቍ**
ሉል ፤ እልማዝ የከበረ ድንጋይ ፤ ከባ ሕር ውስጥ የሚገኝ ሰዳፍ የምትወልደው (ማቴ. 13፥45 ፤ ራእ. 21፥21)።
**ዕንቊባሕርይ - ዕንቊአየኹ**
**ዕንቊአየሽ - ዕንቊዬ - ዕንቊአለች**
**ዕንቊዬነሽ - ዕንቊብርሃን**
**ዕንቊ ሥላሴ** ክርስትና ስም ተመልከት።

735.**ዕድሜዓለም**
ዕድሜ ለሰጠው ማየት ደግ ነው።
ያባት ስም ለገሠ ቢል ይገጥማል።

736.**ዕፀገነት — ዕፀሕይወት**
በገነት ያለች ፍሬ ፤ የሕይወት ፍሬ።
ያባት ስም መድኃኒት ቢል ይገጥማል።

በዚህ ስም ሴቶችም ወንዶችም ይጠሩበታል (ማቴ. 3)።

862. **ዮካብድ** (ዕብ.)
እግዚአብሔር ክብር ነው ማለት ነው።
የሙሴና የአሮን እናት (ዘጸ. 2፥1፤ 6፥20፤ ዕብ. 11፥23)።

863. **ዮዲት** (ዕብ.)
የሜራሪ ልጅ ነች ። ናቡከደነጾር እስራኤልን ሊወጋ ሲል እንዴት እንደተከላከለች የሚገልጽ ታሪክ በመጽሐፈ ዮዲት ውስጥ ተጽፏል (መጽ. ዮዲ 8፥1)።

## - ደ -

864. **ደመቀች - ደመቅሽ**
አበራች፣ ፈካች፣ አማረች ...።
ያባት ስም **ምትኩ** ቢል ይገጥማል።
**ደመቁ - ደመቅሽኝ - ደምቀሻል**

865. **ደመረወርቅ - ደመራሽ**
ወርቅ ጨመረ ማለት ነው።
ያባት ስም ታደለ ቢል ይገጥማል።

866. **ደሚቱ** (አሮ) - **ደሚ -**
ማሬ ፣ ማር ማለት ነው ።
**ደሜ - ደማሜ - ደመወርቅ** (ዐ.ማ)
በቀጥታ ዐማርኛ ትርጉም።

867. **ደሞዜ** (ደመወዜ)
የላቤ ዋጋ፣ ገንዘቤ (ዘሌ. 22፥10)።
ያባት ስም ደረሰ ቢል ይገጥማል።
**ደመወዝ - ደሞዜነሽ - ደሞዝ**

868. **ደራርቱ** (አሮ) - **ደረሬ**
ዘረዘረ (ለአህል) አበበች ፣ ደረሰች ከአዝመራ ጋር የተያያዘ ።
በዚህ ስም የምትታወቀው በ10 ሺ ሜትር የኦሎምፒክ ውድድር ኢትዮጵያን ወክላ በስፔን ፣ ባርሴሎና ከተማ ፣ በአውስትራልያ ሲድኒ ተወዳድራ የወርቅ ሜዳልይ ተሸላሚ የኾነች ኰለኔል ደራርቱ ቱሉ ናት።

869. **ደራሼ**
ድንገቴ ማለት ነው ...።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።

870. **ደስታ - ደሱዬ**
ፍሥሓ ፣ ድርብ እጥፍ የኾነ።
ያባት ስም ታዬ ቢል ይገጥማል።
**ደስታኹን - ደስታዓለም - ደሳለች**

871. **ደብሬ - ደብሪቱ**
ታላቅ ነሽ፣ የክብር ሰው ነሽ ...።
ከፍታ ቦታ ፤ ደብረ ሊባኖስ። ትርጉም፤ የሊባኖስ ተራራ ። ደብረ ጽዮን ዘአፍቀረ ። ትርጉም ፤ የወደደውን የጽዮንን ተራራ (መዝ. 77(78)፥68)።
ያባት ስም ከፍያለው ቢል ይገጥማል።
**ደብረወርቅ - ደብርነሽ - ደብርሽ**
**ደብርዓለም - ደብሯ**
**ደብርሸወርቅ** - የምራት ስም።

872. **ደጅይጥኑ - ደጁነሽ - ደጂቱ**
በደጅ ይቆዩ፣ ይቀመጡ፣ ጊዜ ይሰጥ ...።
ያባት ስም በላቸው ቢል ይገጥማል።

873. **ደግነሽ — ደጊ - ደጊቱ**
ጥሩነሽ፣ ቸርነሽ፣ ርኅሩኅ ነሽ ...።
ያባት ስም ስጦታው ቢል ይገጥማል።

874. **ደግዓለም**
ጥሩ የኾነ ጊዜ፣ ዘመን፤ ዓለም ...።
ያባት ስም ተገኝ ቢል ይገጥማል።



875. **ዱባለች**
ሳትታሰብ መጣች፣ ወረደች ...።
ያባት ስም ፋንታዬ ቢል ይገጥማል።

876. **ዲቦራ** (ዕብ.)
ንብ ማለት ነው ።
የእስራኤል ነቢይትና ዳኛ ነበረች ፤ በጦርነት ጊዜ የጦር አዝማች ፤ በሰላም ጊዜ በፈራጅነት እስራኤልንና እግዚአብሔርን ያገለግሉ ከነበሩት አንዲቷ ነች (መሳ.4)።

877. **ዲና** (ዕብ.)
ፈረደ ማለት ነው።
ልያ የወለደችለት የያዕቆብ ሴት ልጅ (ዘፍ. 30፥21 ፤ 46፥15)።

878. **ዳመነች — ዳመኑ**
ጥሩ ዝናብ ልታመጪ ነው።
ክረምትን ያመለክታል ...።
ያባት ስም በጊዜው ቢል ይገጥማል።

879. **ዳርምየለሽ**
ለቁንጅናሽ ወሰንም፣ ድንበርም የለሽ።
ያባት ስም ዓለሜ ቢል ይገጥማል።
**ዳርእስከዳር - ደሩነሽ - ዳሬነሽ**

880. **ዳባሽ**
ኹሉን የምትፈልጊ ...።
ያባት ስም ሰውነት ቢል ይገጥማል።

881. **ዳኝልኝ**
ፍረጂልኝ ማለት ነው።
ያባት ስም ሞላልኝ ቢል ይገጥማል።
**ዳኛነሽ - ዳኝነት - ዳኝአቸው።**

882. **ዳቶ** (አፋር)
ዐፄ ዮሐንስ ባለቤት ናቸው። የአፋር ልጅ ክርስትና አስጠምቀው ጥበበ ሥላሴ በማሰኘት አግብተው አርአያ ሥላሴን ወለዱ። ለኢየሩሳሌም ገዳም ደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረትን ለማሠራት ብዙ ገንዘብ ረድተዋል።

883. **ዳግማዊት**
ኹለተኛ ማለት ነው።
ያባት ስም ምስክር ቢል ይገጥማል።
**ዳግምብርሃን - ዳግም - ዳግማዊ**

884. **ድልባንቺ**
ባንቺ የተነሳ ድል ተደረገ፣ ተገኘ ...።
ያባት ስም ይበቃል ቢል ይገጥማል።
**ድላረገኝ - ድል-ወንበሯ**

885. **ድርብ**
እጥፍ የኾነች (ሩት. 3፥4)።
ያባት ስም ሀብቴ ቢል ይገጥማል።
**ድርቧ - ድርቤነሽ - ድርብወርቅ**

886. **ድምብላል**
ማጣፈጫ ቅመም ...።
ድንብልብል ያለች የምታምር ...።
ያባት ስም ቅመሙ ቢል ይገጥማል

887. **ድርሻዬነሽ — ድርሻነሽ**
ፋንታዬ ነሽ ...።
ያባት ስም እንዳይከፋኝ ቢል ይገጥማል።

888. **ድባቤ - ድባብነሽ - ድባብሽ**
ከሐር እና ከወርቅ የተሠራ የታቦት ጥላ የወርቅ ዘርፍ ያለው።
ያባት ስም ይመር ቢል ይገጥማል።

889. **ድብቅነሽ — ድብቅ**
ምስጢር፣ ረቂቅ ....።
ያባት ስም ይርጋዓለም ቢል ይገጥማል።

ሴ

የነበረ ቦታ ነው ። መስከረም 10 ቀን ይከበራል (ታአ. ግር.)።

## - ፈ -

971. **ፈለቀች – ፈለቁ**
መነጨች፣ ወጣች፣ አንጸባረቀች፣ በራች
ያባት ስም ጥበቡ ቢል ይገጥማል።

972. **ፈለገብርሃን**
የብርሃን ምንጭ፣ የብርሃን ወንዝ ማለት ነው። **ፈለገጥበብ** -
**ፈለገ ሕይወት** ክርስትና ስም ተመልከች።

973. **ፈለጉሽ**
ይሹሻል፣ ይፈልጉሻል ...።
ያባት ስም እንድነት ቢል ይገጥማል።

974. **ፈረደች**
ዳኝነት ሰጠች ...።
ያባት ስም ግሩም ቢል ይገጥማል።

975. **ፈሰሰወርቅ - ፍሳሴ - ፈሰሰች**
ያባት ስም በለው ቢል ይገጥማል።

976. **ፈቃዱ**
በስዋ ፍላጎት ...።
ያባት ስም እንተነህ ቢል ይገጥማል።
**ፈቃደእምላክ - ፈቀደች - ፈቃድ**

977. **ፈትለወርቅ – ፈትለ - ፈትሏ**
ፈተለ ገመደ ካለው ግስ የወጣ ነው።
ያባት ስም ብሥራት ቢል ይገጥማል።

978. **ፈጠነች – ፈጠኑ - ፈጣን**
በመሄድ፣ በመናገር፣ ቸኩለች፣ ቀለጠፈች
ታላቋን ተከትላ ተወለደች።
ያባት ስም ንጋቴ ቢል ይገጥማል።

979. **ፋሲካ** (ግሪ)
ፍሥሐ፣ ተሻገረ ይኾናል። ፓሳህ ዐለፈ ማለት ነው (ዘጸ. 12፥1)። ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ ዳግም ትንሣኤ ፋሲካ ይባላል። የደስታ ሳምንት ነው።

980. **ፋና – ፋናዬ**
ፏ ብላ የምትታይ ጭለማን የምታርቅ።
ወይም ደግሞ እንደ ፋና የበራች ቀንዲል።
መብራቴ፣ ብርሃንን የምትሰጥ ማለት ነው።
ስለጽዮን ዝም አልልም፤ ስለኢየሩሳሌም ጸጥ አልልም ፤ ጽድቋ እንደ ጸዳል ማዳንዋም እንደ ሚበራ ፋና እስኪወጣ ድረስ (ኢሳ. 62፥1 ፤ ዮሐ. 18፥3)

981. **ፋኖሴ**
መብራቴ፣ ብርሃኔ ፣ እንደ ፋኖስ የምታበሪ፣ ብርሃንን ገላጯ፣ ውብ ቀንዲ ...።
በውስጡ ዘይት የሚጨመርበት እሳቱ በፈትሉ በር ዘይቱን እየመጠጠ ብርሃንን የሚሰጥ መብራት ነው።

982. **ፋንታዬ - ፋንቱ - ፋንታይቱ**
የኔ ድርሻዬ፣ ዕድሌ ...።
ያባት ስም ይበቃል ቢል ይገጥማል።
**ፋንታሽ - ፋንታነሽ - ፋንቱ**

983. **ፋጡማ** (ዐረ. ጉራ.)
በዚህ ስም የምትታወቀው ባለም የማራቶን ሩጫ ውድድር በአሸናፊነት እንደ አበበ ቢቂላ የመጀመሪያዋ ሴት ኢትዮጵያዊት ፋጡማ ሮባ ነች ። ያገሯ ባንዲራ በአትላንታ ኦሎምፒክ ከፍ እንዲል አስደርጋለች ።

984. **ፋጡት** (ጉራ) ምርጤ ማለት ነው።



985. **ፌቤን**
በክንክራኦስ ባለች ቤተ ክርስቲያን ዐሥራት በኩራቷን እያወጣች አገልጋይ የነበረች የቅዱስ ጳውሎስ የስብከተ ወንጌል ረዳት ከነበሩት አንዷ ሴት ነች። እሷም ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መልእክት ይዛ የኼደች ናት (ሮሜ 16፥1)።

986. **ፍሬሕይወት - ፍሬ - ፍሬያት**
የሕይወት ፍሬ ማለት ነው።
መልካም በገነት ውስጥ ያለች (ዘፍ. 3፥7)።
**ፍሬሰላም - ፍሬኹኝ - ፍሬገነት**
**ፍሬሠናይት - ፍሬነሽ - ፍሬወርቅ -**
**ፍሬወይን - ፍሬወይኒ - ፍሬዘር -**
**ፍሬዘውድ -**
ክርስትና ስም ተመልከች።
**ፍሬ ማርያም - ፍሬ ድንግል**
**ፍሬ ኢየሱስ - ፍሬ እግዚእ**

987. **ፍርኦሴ**
ፍርኦስኦስ ያለች ፤ የተምነሸነሸች ፤ ደስ የምትል ማለት ነው።
**ፍርኦስ - ፍርኦሽ - ፍርኖ - ፍርኖስ**

988. **ፍርዳወቀች**
ዳኝነትን ፣ መገላገልን ቻለች ...።
ያባት ስም ዳኛቸው ቢል ይገጥማል።

989. **ፍሥሐ** (ግእ)
ፍሥሐዬ ፣ ደስታዬ ማለት ነው።
**ፍሥሐነሽ - ፍሥሐ-ጽዮን**
**ፍሥሐ ጽዮን** ክርስትና ስም ተመልከች።

990. **ፍቅሬ - ፍቅር**
የኔ ፍቅር ማለት ነው።
ፍቅር የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። የክርስትና ሃይማኖት መሠረት ነው ። ሰው ከሰው ጋራ ሰው ከእግዚአብሔር ጋራ እንዲተባበር ፍቅር ያስፈልጋል (1ዮሐ. 4፥8 ፤ ማቴ. 22፥37- 39፤ ሮሜ. 8፥31-39)።
ያባት ስም እንደገና ቢል ይገጥማል።
**ፍቅረዐዲስ - ፍቅረዓለም - ፍቅርዬ**
**ፍቅረሕይወት - ፍቅርተ - ፍቅሬ**
**ፍቅረሰላም - ፍቅረፀሐይ - ፍቅራይ**

991. **ፍትሕ** (ግእ) - **ፍተዓለም**
ፈትሐ ከሚለው ግስ የመጣ ነው።
ዳኝነትን አየች፤ ፈረደች ...።
ያባት ስም ዳኛቸው ቢል ይገጥማል።

992. **ፍቱንወርቅ**
የነጠረ ፣ የተፈተነ ወርቅ ፤ ፍቱን መድኃኒት እንደ ማለት ።
ያባት ስም ይልሃል ቢል ይገጥማል።

993. **ፍትፍቴ**
ምግቤ ማለት ቢኾን፣ ውበትን፣ ቁንጅናን ያመለክታል።
ያባት ስም ጣፈጠ ቢል ይገጥማል።

994. **ፍኖት** (ግእ)
መንገድ ማለት ነው። **ፍኖተሰላም** ቢል የሰላም መንገድ ። **ፍኖተጽዮን**

995. **ፍጹም**
የበቃ ነውር የሌለባት ፤ ሙሉ የኾነ ጉድለት የሌለባት (ዘዳ 25፥15 ፤ 16፤ ዕብ.5፥14፤ ያዕ.1፥4)። **ፍጹመብርሃን -**
**ፍጹማዊት - ፍጹምነሽ - ፍጹምወርቅ**

ሴ

# ምዕራፍ ፱

## የክርስትና ስሞች (ስመ ጥምቀት)

የክርስትና ስም መነሻው ቅዱስ መጽሐፍ ነው። የብዙኃን አባት የተባለው አብርሃም ይታወቅ የነበረ አብራም ተብሎ ነበር። በኋላ ግን ስምህ አብራም ሳይኾን አብርሃም ይባላል ተብሎ በእግዚአብሔር ተሰየመለት። ይህም ማለት የብዙኃን አባት (የሕዝቦች አባት) የሚል ስም ነው ። ቃል ኪዳኑንም በግዝ ረት አደረገለት፤ ተባረከም (ዘፍ.17፥5 ፤ ሉቃ.1፥59)። በዐዲስ ኪዳን ግን ቃል ኪዳኑ በጥምቀት አደረገ (ሮሜ. 6፥1-11)።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የክርስትና ስም መሰየም የሚገባው በታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትዛዝ መሠረት መኾን አለበት የሚሉ አሉ።

> እንግዲህ ኺዱና አሕዛብን ኹሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኳችኹን ኹሉ እንዲጠብቁ አድርጉ (ማቴ 28፥19)።

አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ጥምቀተ ጸሎቱ የሚከናወነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ስለኾነ በመላእክት በቅዱሳን በጻድቃን ስም መሰየም ጉዳት የለውም ይላሉ ። ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን በተመለከተ በመዋዕለ ትምህርቱ ትዛዝ ሰቷል ።

> እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል። ጻድቅን በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል (ማቴ. 10፥40)።

እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል በማለት በተናገረው ቃል ኪዳን የገባላቸው መላእክት ፣ ጻድቃን ፣ ሰማዕታት ፣ ... በስማቸው ጽላት ተቀርጾላቸው ፤ ቤተክርስቲያን ታንጾላቸው ኦ አምላከ ቅዱስ እገሌ ይባላሉ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ ሲሰየም የኖረው በዚህ አይነት መንገድ ነው። ይህም በጥናት ቀርቧል።

በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመን (1500 – 1533 ዓ. ም) ግራኝ መሐመድ ኢትዮጵያን የእስላም አገር ለማድረግ ክርስቲያንን በጨፈጨፈበት፤ አብያተ ክርስቲያናትን በሚያቃጥልበት ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች በስመ ጥምቀታ



ቸውና በቅዱሳን ስሞች ይጠሩ ነበር። ዋናው የጦርነቱም መነሻ አንዱ ምክን ያት ይህ የክርስትና ስም መጠሪያ ስለነበረ ነው ። ለምሳሌ የዐፄ ልብነ ድን ግል ልጆች ሰበነ ጊዮርጊስ፣ ወለተ ቅዱሳን፣ አመተ ጊዮርጊስ፣ ያዕቆብ፣ ታያ ድራ፣ ወለተ ማርያም ፣ ገላውዴዎስ፣ ሚናስ ፣ ፊቂጦር በመባል በስመ ጥም ቀታቸውና በቅዱሳን ስሞች ይጠሩ ነበር። የራሳቸው የንጉሡ ስም ልብነ ድን ግል (ዕጣነ ድንግል) ተብለው ይጠሩ ነበር። ይህም የሚያሳየው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን እምነት በአማንያኑ ዘንድ በጣም ጠንካራና ጠበቅ ያለ በት ዘመን እንደ ነበረ ነው ። የግራኝ ወታደሮችም ማኅተበ ክርስትናቸውን በመበጠስ፤ ስመ ጥምቀታቸውን እንዲለውጡ ሲያስገድዱ አልለውጥም ያሉ ትን ብዙ ክርስቲያኖች የተጨፈጨፉበት ዘመን ነበር ። ጦርነቱ ከ15 ዓመት በኋላ ሲያበቃ እጨጌ ዕንባቆም ባዘጋጁት መጽሐፈ ቄደር ጸሎት እየተደረገ የንሥሓ ጥምቀት እንዲጠመቁ፤ ጠበል እየተረጩ ስመ ጥምቀታቸውን ወደ ቀድሞው እንዲመለስ ተደረገ።

በጎንደር ዘመን መንግሥት ዐፄ ሱስንዮስ ልጁ ዐፄ ፋሲለደስ ኢትዮ ጵያን በሚያስተዳድሩበት ዘመን ከካቶሊክ እምነት ጋር አለመግባባት ነበረ። ያብዛኛው ሕዝብ መጠሪያ የጥምቀተ ወይም የክርስትና ስማቸው እንደ ነበረና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶና በካቶሊክ ፍኩክር የነበረበት ጊዜ እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል።

የዐፄ ፋሲል ስም የግሪክ ቋንቋ ሲኾን የንጉሥ ልጅ ማለት ነው። በተለያየ ጊዜ ያገቧቸው ሚስቶቻቸው አመተ ድንግል እና እኅተ ክርስቶስ ይባሉ ነበር። ልጆቻቸው ወንጌላዊት ፣ መለኮታዊት፣ ገሊላዊት እና ዮሐንስ ይባሉ ነበር። መንግሥቱን የወረሱት ዮሐንስ ሲኾኑ ጸሎተኛ ፣ ይቅርባይ ስለ ነበሩ ጻድቁ ዮሐንስ ይባላሉ።

አኹን ባለንበት ዘመን በተመሳሳይ የፕሮቴስታንት አማንያን ይልቁ ንም የጴንጠቆስጤ አማንያን በኢትዮጵያ በመስፋፋታቸው ምክንያት በክርስ ትና በኢትዮጵያውያን ስሞች መጠራት ቀርቶ ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተ ጠቀሱ ስሞች ላይ ብቻ ትግል በማድረግ ኹሉም በፍርሐት እና በሽቅድም ድም ወደዚያው ያተኰረ ይመስላል።

### (ሀ) የሚያከራክሩ የክርስትና ስሞች

ከላይ እንደተገለጸው ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የሚያከራክሯቸው ነጥቦች አሉ ፤ የመልአክትን ወይም የቅዱሳንን ስም ወስዶ ያለቅጽል መጥራት ባለ ቤትነትን እንደመቀማት ወይም እንደ መውሰድ ይኾናል በማለት ሊቃውንተ

ቤተክርስቲያን ይናገራሉ። በአንዳንድ ሊቃውንት ዘንድ ያለ ቅጽል የተሰየሙ የክርስትና ስሞች አሉ ።

ስመ ክርስትና ሲሰየም በፈጣሪ፣ በስመ ቅዱሳን፣ በስመ መላእክት፤ በስመ ሰማዕታት ስም ቅጽል ተጨምሮበት ነው ። ያለቅጽል በቁሙ ስምን ብቻ መጥራት የኦርቶዶክሳውያን ባህል አይደለም። በቀጥታ ሚካኤል ፣ (ማይክል)፣ ገብርኤል፣ ጊዮርጊስ (ጆርጅ)፣ ማርያም (ሜሪ) ሌሎችም በነጠላ መጥራት የምዕራባውያን (የፕሮቴስታንት) ባህል ነው። ሚካኤል ተብለው የሚጠሩ ብዙዎች አሉ። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ንጉሥ ሚካኤል አሊ አንዱ ናቸው። የክርስትና አባታቸውም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዮሐንስ ነበሩ ይህንን ተከትሎ ሊኾን ይችላል ብዙ ሰዎች ሚካኤል የሚለውን በመጠሪያ ስምነትም ሲጠሩበት ይሰማል ። ገብርኤል ተብሎ ሲጠራ ግን ብዙ አይሰማም። በነጠላው ያለቅጽል ሚካኤል ፣ ገብርኤል ተብለው የሚሰየሙት ጳጳሳት ብቻ ናቸው ።

መሐልየ መሐልይ ዘሰሎሞን ወይም ከመዝሙር ኹሉ የሚበልጠው የሰሎሞን መዝሙር (መሐ. ዘሰ. 1፥1) በምሳሌነት የተሞላ ነው። በምሳሌነት የተነገረው ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነው። ዐፀደ ወይን ፣ እምሳለ ወርቅ ፣ አስካለ ወይን (የወይን ፍሬ) በማለት ያነሳል ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በጽጌ፣ አበባ ትመሰላለች። ምእመናንም ጽጌ፣ ጽዮን፣ አስካለ ፣ ዐፀደ ወይን ተብለው ይጠራሉ። ብዙዎች ምእመናን ሲጠሩበትም ኖረዋል።

ቅድስት ድንግል ማርያም የሚለው ስሟ ግን የባሕርይ ስሟ ነው። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ወላዲተ አምላክ ነች። ይህም የባሕርይ ስም ስለኾነ ቅጽል በመጨመር ካልኾነ ሊወረሰና ሊጠሩበት አይገባም።

የክርስትናን ስም ሲጠሩበት ትርጉም የሚሰጥና አንደበትን ወይም አፍን ያዝ የማያደርግ በቅዱሳን መጻሕፍት መሠረት ምስጢር ሊገለጽ የሚችል ቅጽል ተጨምሮበት መሰየም አለበት።

ለምሳሌ መንበረ ፀሐይ ተብሎ ስም አይጠራም። ስመ መካን (የቦታ ስም) የእንጦጦ ማርያም የደብር መጠሪያ ስም ስለኾነ ለክርስትና የመጠሪያ ስም አይኾንም ። ሌላም መንበረ ጸባዖት ተብሎ አይሰየምም ። እንዲሁም ደግሞ ስመ ሀገር የክርስትና ስም ሊኾን አይገባም። ወለተ እስራኤል፣ ወለተ ኢትዮጵያ ፣ ወለተ ቍስቋም ተብሎ አይሰየምም።

መንበረ ማርያም ተብሎ ሊሰየም ግን ይችላል ። ሲጠሩት ስሜት የሚሰጥ፤ ምስጢርና ትርጉም ያለው ሊኾን ይገባል።



የመጠሪያ ስም ወላጆች መጠሪያ ስም ከሰየሙ በኋላ ከአርባና ከሰማኒያ ቀን ወይም በማንኛውም ጊዜ ለሚጠመቅ ከእግዚአብሔር ልጅነትን ለማረጋገጥ የተለየ የስም ስያሜ ይደረጋል። ካህኑና የክርስትና አባት ወይም እናት እንዲሁም ወላጆች ከተቻለ ተነጋግረው መርጠው ልጃቸው በስለት የተገኘ(ች) ከኾነ ስመ ክርስትና (የመጽሐፍ ስም) በመረጡት ቅዱስ ስም ይህ ይኹንልን ማለት ይችላሉ። የክርስትና ስም ከተሰየመ በኋላ ስምክ ይኩን... እገሌ ... እያለ የሚያውጀው ካህኑ ነው ።

የሕይወት መጽሐፍ ወይም የመጽሐፍ ስም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመዘገበ ነው (ዘጸ.32፥32 ፤ ዳን.12፥1 ፤ ሉቃ.10፥20 ፤ ፊል.4፥3፤ ራእ.3፥5 ፤ 20፥12 ፤ 21፥27)።

የክርስትና አባትና እናት መኾን ከዝምድና ሐረግ ገብቶ ይቆጠራል። ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እና ለቲቶ የመንፈስ ቅዱስ አባታቸው እነሱ ደግሞ ፍጹም ልጆቹ ነበሩ (2ኛ. ጢሞ. 2፥1) ።

ወላጆችም ይህንን ኀላፊነት የሚረከብ ሰው ልጁ ሳይወለድ በፅንስ ሳለ ይመርጣሉ ። ወይም በተዘዋዋሪው ዝምድናውን ወዳጅነቱን የፈለገ ቤተሰብ አስቀድሞ ክርስትናውን ለማንሳት እና ቤተ ዘመድ ለመኾን ዝምድናውን እንፈልገዋለን በማለት ቤተሰቡን መለመንና ፍቃዳቸውን መጠየቅም የተለመደ ነው። ወይም ባልና ሚስት ተመካክረው ምርጫ ያደርጋሉ ።

ወላጆች (ባልና ሚስት) ከወለዱ በኋላ ወንድ ወይም ሴት መኾኑን ካረጋገጡ ለመረጡት ሰው ክርስትናውን ይሰጣሉ ።

ክርስትናው የተሰጣቸው ሰዎችም ዝምድናውና ኀላፊነቱ የጋራ መኾኑን በመረዳት አክብረው በደስታ በመቀበል ሕፃኑ ሲጠመቅ ጣት በመያዝ ከልጄ አለየውም፤ እንደ ልጄ አድርጌ እጠብቀዋለኹ ፤ ሃይማኖቴን አስተምረዋለኹ በማለት ቃል ኪዳን በእግዚአብሔር ፊት ይገባሉ። ሕፃኑ ከተጠመቀ በኋላ በገዙለት ዐዲስ እና ንጹሕ ፎጣ ጠቅለው ከካህኑ ተቀብለው ያቅፋሉ። ዝምድናውም ከሥጋዊ ዝምድና የበለጠ የሚኾን እንጂ አይተናነስም። በክርስትና ቤተሰብ የተሳሰረ በጋብቻም፣ በሌላ ነገር እንደ ሥጋዊ ዝምድና ዘር ይቆጠርለታል። በዚህ ዝምድና የተሳሰሩ ኹሉ ከሥጋዊ ዝምድና የበለጠ ስለኾነ መጥፎ ነገር አይተሳሰቡም።

የክርስትና አባትና እናት (አበልጅ) ከዝምድናው ባሻገር ዋና ዓላማው

ለሃይማኖቱ ኀላፊ በመኾን ሕፃኑ በሃይማኖት በእምነት እንዲያድግ ለማስ ተማር ኀላፊነትን ለመውሰድም ነው ። በዓመታዊ በዓላት ጊዜ ለልጁ ብሎ ዐዲስ ልብስ መግዛት ፤ ልዩ ልዩ ስጦታ መስጠት፤ ማፍቀር የአበ ልጅ ተግባር ነው። ልጆችም የክርስትና አባት ወይም እናት የሚያመጡላቸውን ፤ የሚያደርጉላቸውን በናፍቆትና በጉጉት ይጠብቃሉ። ይህ ሥርዐት ከቀድሞ ጀምሮ የክርስትና ወላጆች ሲያስተምሯቸው ስለ መልካም አስተዳደጋቸው ሲጠነቀቁላቸው፤ ባጠቃላይ ስለኑሯቸው ኹሉ ሲያስቡላቸው ይኖሩ ነበር።

የክርስትና አባትና እናት ክርስትና ያነሱትን ልጃቸውን በኑዛዜ ጊዜም እንኳን ከልጆቻቸው አይለዩዋቸውም ። ምክንያቱም በእግዚአብሔር አገልጋዩ ካህን ቄስ ፊት ቃል ኪዳን ሲገባ ሕፃኑን ሲረከብ ፤ ከበኲር ልጅህ እንዳትለይ ፣አስተምር፣ ዳር፣ ኳል ስለተባለ እሱም ቃል ኪዳን ስለገባ ይህንን ይፈጽማል ማለት ነው። ሕፃኑም ካደገ በኋላ የክርስትና አባቱን ልክ እንደ አባቱ አድርጎ ያከብራል፤ ትዛዙንም ይሰማል ። ይህ ከቀድሞ ጀምሮ ሲኖር ሲተካ እዚህ ደርሷል ማለት ነው።

በሌላ መልኩ ወላጆች በስለት የተወለደ ከኾነ ወይም ደግሞ ራሳቸው ሕፃኑን በሃይማኖት ለማሳደግ ኀላፊ ኾነው ለታቦት ይሰጥልኝ በታቦቱ ስም ይነሳልኝ ይላሉ። ይህም ማለት ቤተ ክርስቲያን እና ወላጆች ኀላፊነቱን ይወስዳሉ ማለት ነው ። ነገር ግን ከዚህ ይልቅ ወላጆች የክርስትና አባትና እናትን ቢመርጡ ዝምድናም ማጠንከር እንዲሁም ልጆችን በማሳደግ መረዳዳትም ቢኖር ጠቀሜታ ይኖረዋል ።

የክርስትና ስም ቅጽሉ ከስሙ ተነጥሎም መጠሪያ ይኾናል ። ለምሳሌ ገብረ እግዚአብሔር የተባለው ሰው በአጭሩ ገብሬ ፤ ሀብተ ማርያም የተባለው ደግሞ ሀብቴ ተብሎ ሊጠራ ይችላል ማለት ነው ።

እሥራ ኹለቱንም ወራት ከመስከረም ወር አንስቶ የወር በዐላት እና የዓመት በዐላት አሉ። በዚህ ጊዜ የተወለደ ወይም የሚጠመቅ ልጅ ዕለቱን በተመለከተ በማያያዝ ስም ይሰየምለታል ማለት ነው ። ስለዚህም በታሪክ ኢትዮጵያውያን ሲጠሩበት የኖሩት ስሞች ተሰብስበው ቀርበዋል ።



## (ሐ) የወንዶች የክርስትና ስሞች

### - ፩ -

**ልደታ ማርያም ፣ ኤልያስ ፣ ዮሐንስ ፣ ራጉኤል**

በመስከረም ፩ ዓውደ ዓመት
ራጉኤል፤ ሐዋርያው በርቶሎሜዎስ፤ ኤልያስ። ግንቦት ፩ ቅድስት ድንግል ማርያም ልደት ።

### - ፪ -

**ልደተ ዮሐንስ መጥምቅ፤ ታዴዎስ**

መስከረም ፪ መጥምቁ ዮሐንስ አንገቱ የተሰየፈበት፤ በታኅሣሥ ፪ በሰንክሳር እንደተገለጸው ሠለስቱ ደቂቅ ከእሳት የዳኑበት፤ እንዲሁም ሐዋርያ ታዴዎስ ይከበራል።

**መጥምቀ መለኮት**
**መጥምቁ ዮሐንስ**

### - ፫ -

**በዐታ ለማርያም ፣ ፋኑኤል መልአክ ፣ ዜና ማርቆስ**

እበው ቤተከ ምስለ መባዕየ ።
ወእሁብ ብፅዐትየ ዘነበብኩ በአፉየ ።
ትርጉም፤ ከመባ ጋር ወደ ቤትህ እገባለኹ። በመከራዬ ጊዜ በአፌ የተናገርኹትን ። ከንፈሮቼም ያሉትን ስእለቴን (መዝ. 95፥13)።
ታኅሣሥ ፫ በዐታ ለማርያም ፤ ፋኑኤል አብሮ ይከበራል ።

**ብፅዐተ ማርያም**
**ስብሐተ ፋኑኤል**

### - ፬ -

**ዮሐንስ ወንጌላዊ (ወልደ ነጐድጓድ)**

ወተመዪጦ ጴጥሮስ ርእዮ ለዝኩ ረድእ ዘያፈቅሮ እግዚእ ኢየሱስ እንዘ ይተልዎ፤ ወውእቱ ረድእ ፤ ትርጉም ፤ ጴጥሮስም መለስ ብሎ ያን ጌታ ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ሲከተለው አየ (ዮሐ. 21፥20፤ 13፥23)።

ጥር ፬ ሐዋርያው ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ፤ ታኅሣሥ ፬ ሐዋርያው እንድርያስ ይከበራል ።

**ብርሃነ ዮሐንስ – መዝገበ ዮሐንስ**
**ተስፋ ዮሐንስ – ተክለ ዮሐንስ**
**አርአያ ዮሐንስ**

**ክፍለ ዮሐንስ**
ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ሳልሣዊ 1921 -1993 ዓ.ም. የነበሩት ከጵጵስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው ክፍለ ዮሐንስ በመባል ይታወቁ ነበር። የወሎ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ነበሩ።

**ወልደ ዮሐንስ**
መልአከ ብርሃናት ወልደ ዮሐንስ በቦሩ ሜዳ ከሦስት ልደት ባዮች ጋር ይከራከሩት ከነበሩት አንዱ በስመ ጥምቀታቸው ወልደ ዮሐንስ በመባል ይታወቃሉ ።

**ዐምደ ዮሐንስ**

**ዐርከ ዮሐንስ**
እጨጌ ዐርከ ዮሐንስ ዘሰጋ (1814 - 1815 ዓ.ም.) በስም ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

ወ.ክ

መድኀኒዓለም የተሰቀለበት (ጥንተ ስቅለት) ነው ። ጥር ፳፪ ሱርያል (ሲቃነ መላእክት) ይከበራል።

**ሠርጸ መድኅን — ተወልደ መድኅን**
**ገብረ መድኅን**

## ክርስቶስ

ከመ ኢይንግሩ ለመኑሂ ከመ ውእቱ ክርስቶስ
ትርጉም፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኾነ ለማንም ለማን እንዳይናገሩ አዘዛቸው (ማቴ.16፥21)።

**ማኅደረ ክርስቶስ - ልሳነ ክርስቶስ**
**ሕላዌ ክርስቶስ — ሕንጸ ክርስቶስ**

**መልከዓ ክርስቶስ**
አቡነ መልከአ ክርስቶስ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

**መርሐ ክርስቶስ**
ብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ የመቀሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እንዱኹም የሊቃውንት ጉባኤ ዋና ሰብሳቢም ነበሩ። የጵጵስና ስማቸው ስመ ጥምቀታቸው የነበረ ሲኾን የመጠሪያ ስማቸው ያሬድ ገርማይ ነበር ።

**መርዓዌ ክርስቶስ — መብዓ ክርስቶስ**

**መዝሙረ ክርስቶስ**
አቡነ መዝሙረ ክርስቶስ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

**መዝራእተ ክርስቶስ**
አቡነ መዝራእተ ክርስቶስ በ15ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

**ማኅተመ ክርስቶስ**

**ሠምረ ክርስቶስ**
አቡነ ሠምረ ክርስቶስ በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አበምኔት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

**ሠርጸ ክርስቶስ — ሥዕለ ክርስቶስ**

**ሰፋኒ ክርስቶስ**
እጨጌ ሰፋኒ ክርስቶስ በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር (1683 ዓ.ም- ኅዳር)።

**ተንሥአ ክርስቶስ — ተላዌ ክርስቶስ**
**ተሰፋ ክርስቶስ — ተወልደ ክርስቶስ**
**ቃለ ክርስቶስ — ብርሃነ ክርስቶስ**

**ንዋየ ክርስቶስ**
ዐፄ ንዋየ ክርስቶስ ስመ መንግሥታቸው ሰይፈ አርዕድ ይባላል፤ በዚህ የክርስትና ስም ይጠሩና ይታወቁ ነበር።

**ኃይለ ክርስቶስ**
በአንኮበር የመስጫ ማርያምን ገዳም የመሰረቱ አባ ኃይለ ክርስቶስ በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይታወቃሉ።

**ኀረየ ክርስቶስ — አባለ ክርስቶስ**
**አካለ ክርስቶስ — አምኃ ክርስቶስ**
**እስትንፋሰ ክርስቶስ - እኅወ ክርስቶስ**
**እደ ክርስቶስ — ወልድ ክርስቶስ**

**ዘክርስቶስ**
የደንከላ እጨጌ ዘክርስቶስ (1660 ዓ.ም) በመባል በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር

**የማነ ክርስቶስ**



**ገብረ ክርስቶስ**
ዐፄ ላሊበላ ስመ መንግሥታቸው በጥምቀት ስማቸው ገብረ ክርስቶስ በማለት ተጠርተውበታል ።

እንዲሁም ደግሞ የንጉሥ ቴዎዶሮስ ልጅ ጸድቁ ገብረ ክርስቶስ የሚጠራው በስመ ጥምቀቱ ነው። በዐረብኛ ሲተረጎም አብደል መሢሕ ይኾናል።

**ግርማ ክርስቶስ**

**ጸጋ ክርስቶስ**
እጨጌ ጸጋ ክርስቶስ ዘቤተልሔም በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።
**ፍቅረ ክርስቶስ — ፍሥሓ ክርስቶስ**

## አልፋ

አነ ውእቱ አልፋ ወኦ።
አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ (ራእ.1፥8 ፤22፥13)።

**ተክለ አልፋ**

## - ፳፰ -

### ዐማኑኤል

ወናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ወይሰመይ ስሙ ዐማኑኤል ።
ትርጉም ፤ እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙም ዐማኑኤል ይባላል (ኢሳ. 7፥14 ፤ ማቴ. 1፥23 ፤ ሉቃ.1፥31)።

ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ገና ይባላል (ልደት) በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን መዋሉ ቀርቶ በዚህ ቀን ይውላል ።

**ብርሃነ ዐማኑኤል — ወልደ ዐማኑኤል**
**ዘዐማኑኤል — ገብረ ዐማኑኤል**

## ሰንበት

መጽአ ላእሌየ መንፈስ በዕለተ ሰንበት እሑድ ወሰማእኩ ቃለ ዐቢየ (ራእ.1፥10)
**ገብረ ሰንበት**

**ወልደ ሰንበት**
የታወቁት ያቋቋም መምህር የነበሩት አለቃ ወልደ ሰንበት በስመ ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር ።

## አምላክ

እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ።
(ዘጸ. 20፥1)
**መዝገበ አምላክ — ብርሃነ አምላክ**
**ወልደ አምላክ — ዘአምላክ**
**ገብረ አምላክ — ፈቃደ አምላክ**

## - ፳፱ -

### በዐለ ወልድ (ትስብእት)

### ወይም በዐለ እግዚእ

ወወለደት ወልደ ዘበኵራ ወአሰረቶ መንኮብያቲሁ ፤ ወጠብለለቶ በአፅርቅት ፤ ወአስከበቶ ውስተ ጎል ፤ እስመ አልቦሙ መካን ውስተ ማኅደሮሙ።
ትርጉም ፤ የበኩር ልጇንም ወለደችው አውራ ጣቱንም አሰረችው ፤ በጨርቅም ጠቀለለችው፤ በበረትም አስተኛችው ፤ በማደሪያቸው ቦታ አልነበራቸውምና (ሉቃ. 2፥7)።

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ። በሰግር ዓመት በዘመነ ዮሐንስ ታኅሣሥ ፳፰ ይኾናል። መጋቢት ፳፱ ደግሞ ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን የፀነሰችበት ዕለት ነው ።

**ሀብተ ወልድ — ማኅተመ ወልድ**
**ቃለ ወልድ — ገብረ ወልድ**
**ተክለ ወልድ**

**አካለ ወልድ**
በዚህ ስም ኢትዮጵያዊው የነገረ መለኮት ሊቅ መምህር አካለ ወልድ በመባል ሊታወቁ ። ያረፉበት ዘመን ኅዳር 9 ቀን 1912 ዓ.ም. ነው።

**ተወልደ መድኅን**
እጨጌ ተወልደ መድኅን ዘአዘዞ በስም ጥምቀታቸው ይጠሩ ነበር።

**ተወልደ ብርሃን**
ጥቅምት18 ቀን 1983 ዓ.ም. የመላው የኢትዮጵያ ገዳማት ኢጲስ ቆጶስ ተብለው የተሾሙት ብፁዕ አቡነ ፊልጶስ በቀድሞ ስማቸው ይታወቁ የነበሩት አባ ተወልደ ብርሃን በሚል ስመ ጥምቀታቸው ነበር።

**ማኅተመ እግዚእ - ቃለ እግዚእ**
**በረከተ እግዚእ - ወረደ እግዚእ**
**ዐቢየ እግዚእ - ዕቍበ እግዚእ**
**ዘርዐ እግዚእ - ዘመድኅን**
**ያፍቅረነ እግዚእ - ገብረ እግዚእ**
**ጥበበ ወልድ**

**ፈቀደ እግዚእ**
በኢየሩሳሌም ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ገዳም አበምኔት (1895 - 1898 ዓ.ም) በስመ ጥምቀታቸው አባ ፈቀደ እግዚእ ተብለው ይጠሩ ነበር። የተሾሙትም በዐፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነበረ።

**ፍቁረ ወልድ**

**- ሑ -**

**ሐዋርያው ቅ. ማርቆስ**
ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ።
ትርጉም ፤ ቃላቸው እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ (መዝ. 18፥3)
**ወልድ ማርቆስ**

**ዜና ማርቆስ**
በዐፄ ይኩኖ አምላክ ዘመን ይኖሩ የነበሩት የምሪት መምህር በስመ ጥምቀታቸው አቡነ ዜና ማርቆስ በመባል ይታወቃሉ።

**ትንሣኤ**
ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ ወይቤሎሙ ንሥትዎ ለዝንቱ ቤተ መቅደስ ወበሠሉስ ዕለት አነሥኦ ።
**ትርጉም** ፤ ጌታ ኢየሱስም ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስተኛውም ቀን አነሣዋለኹ ብሎ መለሰላቸው ፤ ቤት ስለ ተባለው ሥጋው ነገራቸው (ዮሐ. 2፥19 ፤ 20፥1 ፤ ማቴ 26፥ 61)።

**ብርሃነ ትንሣኤ - ትንሣኤ ክርስቶስ**
**ትንሣኤ ኢየሱስ**

**ወልደ ትንሣኤ**
ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ቀዳማይ (1911- 1989 ዓ.ም.) ከጵጵስና በፊት በስመ ጥምቀታቸው **ወልደ ትንሣኤ** በመባል ይታወቁ ነበር። ሀብተ ፈውስ ተሰጥቷቸው በወሊሶ ብዙ ህመምተኞችን እያጠመቁ ፈውሰዋል።

**ዘፈረ ብርሃን — ገብረ ትንሣኤ**

**በዕርገት**
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሥራውን ጨርሶ ወደ ሰማይ ዐረገ (የሐ. ሥራ1፥6 ፤ ሉቃ. 24፥50)።

**ዕርገተ ቃል - ዕርገተ እግዚእ**
**ዕርገተ ኢየሱስ - ዕርገተ መድኅን**



**ቃል**
ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ወውእቱ ቃል ኀበ እግዚአብሔር ውእቱ፤ ወእግዚአብሔር ውእቱ ቃል
**ትርጉም** ፤ ያ ቃል ቀዳማዊ ነው ፤ ያ ቃል በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበረ ፤ ያ ቃል እግዚአብሔር ነው (ዮሐ.1፥1 ፤ 17፥5 ፤ ዘፍ.1፥1 ፤ 1ኛዮሐ. 1)።

**ልዑለ ቃል - መዝገበ ቃል**
**ወረደ ቃል - ብርሃነ ቃል**
**ኀይለ ልዑል - ነቢየ ልዑል (ዮሐንስ)**

**ጳጉሜ ፫**
**ሩፋኤል**
ከከበሩ ከመላእክት አንዱ ሩፋኤል ነው (መጽ. ሄኖ. 6፥3)።

**በብሐተ ሩፋኤል - ኀይለ ሩፋኤል**
**ወልደ ሩፋኤል**

ከዚህ በላይ ያሉት የክርስትና ስም እንዱሁም የመጠሪያ ስም ኾነው ያገለግላሉ ። ከበድ ያሉትን እና ትርጉም የሚያስፈልጋቸውን የግእዝ ቅጽል ትርጉም ችም በመጠሪያ ስም ተተርጕሟል ።

**ማሳሰቢያ፦**

በግእዝ ወለተ ማርያም የሚለው ቅጽል በትግርኛ ባህል በአንዳንድ ቦታ ለተ ማርያም ይላሉ። በዚህ ጽሑፍ ግን በግእዙ በመሠረታዊው ቋንቋ ተጽፏል ። እንዲህ አይነቱ ስሕተት በቋንቋ የተለመደ ነው። ለምሳሌ፡- በግእዝ ገብረ እግዚአብሔር የሚለውን በዐማርኛም ገበረእግዚያር፤ ገብረ መድኅን ከማለት ገብረመድኅን ማለት የተለመደ ነው ። ስለዚህ ኹሉም በግእዙ መንገድ ተስተካክለው ቀርበዋል ። በዚህ ውስጥ ያልተካተቱ የክርስትና ስሞች አሉ ይህ ግን ለመነሻነት ቀርቧል።

**ወ.ከ**

# ምዕራፍ ፲

## የማዕርግ ስሞች (ስመ ተቀብዖ)

የማዕረግ ስሞች እነዚህም፦ ያክብሮት ፣ የሙያ፣ የሥልጣን፣ የክህነት የቤተ መንግሥት፣ የወታደር ስሞች ፤ ከመጠሪያ ስሞች ኋላ እየገቡ ዋናውን ስም ያደምቁታል ፤ አንዳንዴም ብቻቸውን መጠሪያ በመኾን ያገለግላሉ ።

### (ሀ) ጳጳሳት ቅብዐ ክህነት ሲቀቡ የሚሰየሙት ስሞች

ጳጳስ ቃሉ በግሪክ ቋንቋ ሲኾን ትርጉም ጠባቂ (እረኛ)፣ ተቆጣጣሪ የሃይማኖት መሪ ማለት ነው። መነኰሳት ከሚኖሩበት ገዳም ወይም ደብር በምግባራቸው ፣ በጸሎታቸው፣ በዕውቀታቸው ለዚህ ማዕረግ ተመርጠው ሲበቁ ፤ ዐዲስ የሐዋርያነት የብፅዕና ስም ይሰጣቸዋል ።

በጠባቂነት የነበሩትን አባቶች ሐዋርያትን ከዚያም ተላዊ ሐዋርያት ኾነው ያለፉትን አባቶች ፤ የቅዱሳንን ፤ ያለፉ አባቶች ስም ይወርሳሉ ። ውርርሱም ቀዳማዊ ፤ ዳግማዊ ፤ ሣልሳዊ እየተባለ ይቀጥላል እንጂ አይቋረጥም ማለት ነው ።

ቅዱስ ጴጥሮስ ሊቀ ሐወርያት ተብሎ ከመጠራቱ በፊት ስምዖን ነበር ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የጠባቂነት ማዕረግ ሰጥቶት ጴጥሮስ ብዬሀለሁ ብሎታል። ከዚያም አንተ ብፁዕ ነኽ አለው ። ጳጳሳት ሲመረጡ የቀድሞው የመጠሪያ ስማቸውን ይቀየራል ። በምትኩም የሐዋርያት ስም ወይም የሐዋርያት ተከታይ የነበሩ አባቶች ስም የቅዱሳን ስም ይሰጣቸዋል ማለት ነው።

ይህም የብፅዕና ሥልጣን የተለየ ንፁሕ ፤ መንፈሳዊ የታመነ ፤ ሠራውና ልቡናው የቀና ፤ ቸር ፣ ብእሴ እግዚአብሔር የኾነ የበጎች ጠባቂ ይኾናል (ዮሐ. 1፥42 ፤ ማር. 16፥18)። ብፁዕ የመባል ትርጉሙም፤ ክቡር፣ ምስጉን፣ ምሩቅ፣ በክቡር እና በቅዱስ መካከል ያለ ማለት ነው።



እንደዚሁም ከጠባቂዎች ሊቃነ ጳጳሳት መካከል የጴጥሮስን ቦታ የሚይዝ የአባቶች አባት ማለትም በትረ-ያርክ ይመረጣል (በግሪክ ፓትሪአርኽ) ይህም ማለት ሊቀ ጳጳስ የሲኖዶሱ መሪ ቀዳሚ የሚኾን ከንቱ ውዳሴ የሌለበት ደግ አባት ፣ ኀዳጌ በቀል የሌለበት (ይቅር የሚል) ማለት ነው ። በዚህ መሠረት የሊቃነ ጳጳሳት ጉባኤ ሲኖዶስ ዐዲስ ጳጳሳት ስም እየሰየመ ይመርጣል (ሰንክሳር መጋ 13፥ ታኅሣ. 1)።

<u>ለምሳሌ፦</u>
ሐምሌ 18 ቀን 1940 ዓ. ም. ሲመተ ጵጵስና የተፈጸመላቸው እምስቱ የኢትዮጵያ ጳጳሳት።

■ **አቡነ ባስልዮስ**
የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ናቸው። ሊቀ ጳጳስ ከመኾናቸው በፊት የመጀመሪያ የመጠሪያ ስማቸው ። እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ነበር ።

■ **አቡነ ሚካኤል**
የመጀመሪያ ስማቸው መምህር ገሪማ ወልደ ኪዳን በመባል ይታወቁ ነበር።

■ **አቡነ ቴዎፍሎስ**
መጠሪያ ስማቸው ሊቀ ሥልጣናት መልእክቱ ወልደ ማርያም በመባል ይታወቁ ነበር።

■ **አቡነ ያዕቆብ**
መምህር ዘፈረ ብርሃን ገብረ ጻድቅ ይባሉ ነበር ።

■ **አቡነ ጢሞቴዎስ**
የመጠሪያ ስማቸው ጌታኹን ወልደ ሐዋርያት (መምህር) ይባሉ ነበር ።

■ **እጨጌ የሚለው ስም ታሪክ።**
ከጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ማንኛውንም አስተዳደር የሚመራ በደብረ ሊባኖስ በአቡነ ተክለሃይማኖት መንበር የሚቀመጥ ነው። አቡነ ተክለ ሃይማኖት በወላሞ ሞተሌሚ የሚባለውን ንጉሥ አስተምረው ከአረመኔነት ወደ ክርስትና መለሱት። ከዚህ በኋላ እጨጌ አሏቸው። በወላሞ ቋንቋ ጨጋ ማለት በጣም የከበረ ሰው ማለት ነው። ከዚያ ተያይዞ የመጣ ሥርዓት የደብረ ሊባኖስ ገዳም እጨጌ እየተባለ በአስተዳደሩ ኹሉ ተጠሪ ፣ ተጠያቂ ኾኖ ኖረ ።

ማ

## (ለ) ሥልጣነ ክህነት እና ያስተዳደር የማዕርግ ስሞች

### (፩) የደብር አለቆች የማዕርግ ስም

ቀደም ባሉ ዘመናት ለታላላቅ ደብር የሚሾሙት አለቆች በነገሥታቱ ትዛዝ ጭምር በማዕርግ ይሾሙ ነበር።

- ንቡረ እድ — የአክሱም እና የዐዲስ ዓለም አለቃ።
- ጸባቴ — የደብረ ሊባኖስ የገዳሙ አስተዳዳሪ ያገሩ ተጠሪ ምስለኔ ነው።
- ሊቀ ሊቃውንት — የበአታ ገዳም አለቃ ። የአለቆች አለቃ ።
- ሊቀ ሥልጣናት — መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ አለቃ።
- ሊቀ ካህናት — የካህናት አለቃ ፤ ሹም።
- መልአከ ብርሃን — የደብረ ብርሃን ቅ. ሥላሴ አለቃ ።
- መልአከ ሰላም — የእስጢፋኖስ አለቃ ።
- መልአከ ገነት — የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ አለቃ።
- መልአከ ፀሓይ — እንጦጦ መንበረ ፀሓይ ቅድስት ማርያም አለቃ።
- አለቃ — መሪ ፣ አስተዳዳሪ ማለት ነው።
- መምህር — አስተማሪ አለቃ ማለት ነው።

ደብሩ ኹሉ የራሱ መጠሪያ ስላለው ለመግቢያ ያህል ለምሳሌነት ይህ የተገለጠው በቂ ነው ።

### (፪) በደብር የክህነት አገልግሎት የማዕርግ ስሞች

- **መምሬ**

ሕግ ጠብቆ የሚኖር፤ የምእመናን መሪ፣ አስታዋሽ፣ አስተማሪ፣ ዘካሪ፣ የንስሐ አባት፣ ቀድሶ የሚያቆርብ፣ እምዋ ጠምጥሞ ጎላ ብሎ የሚታይ፤ ግርማ ሞገስ የተሞላ። የጸዋትወ ዜማ መምህር ሌሎችም ዕውቀቶች ሊኖሩት ይችላል።

- **ቀሲስ (ግእ) ቄስ (ዐማ)**

ተዘከረኒ ኦ እቡየ ቀሲስ ፤ (ቅዳ) ቀሰ አገለገለ ከሚለው ግስ የመጣ ነው ። ከመምሬ ጋር ተመሳሳይ ነው።

- **ቄስ ገበዝ (ጎበዝ)**

ብርቱ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ ፤ የሰሞነኞች አለቃ ፤ ምስጢር ዕቃ ጠባቂ ፤ የመንበር ቁልፍ በእጁ የኾነ ። ባለ አደራ ታማኝ ።



- **ሊቀ ዲያቆናት**

ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ እስጢፋኖስ ሊቀ ዲያቆን የዲያቆናት አለቃ ኾኖ ተሾሞ ነበር። በዚያ መሠረት የዲያቆናት አለቃ ታማኝ ፣ ንፁሕ፣ ግብረገብ ፣ ትጉህ ለሃይማኖቱ ቀናኢ የኾነ (የሐ. ሥራ. 6፥5)።

- **ዲያቆን**

ለተልእኮ የሚፋጠን የቄስ ረዳት የምእመናን አገልጋይ።

### (፫) የአብነት ትምህርት ቤት መምህራን የማዕርግ ስሞች።

- መጋቤ ምስጢር — የቅኔ መምህር።
- መጋቤ መዝሙር — የዝማሬ መዋሥዕት ያቋቋም መምህር።
- መጋቤ ብሉይ — የብሉይ ኪዳን መምህር።
- መጋቤ መምህራን — የሊቃውንት መጻሕፍት መምህር።
- መጋቤ ምክር — የመጽሐፍተ መነኰሳት መምህር።
- መጋቤ ስብሐት — የምዕራፍ እና የጾመ ድጓ መምህር።
- መጋቤ ላእከን — የፊደል ንባብ መምህር።

### (፬) የሊቅነት ፣ የመዘምርነት የማዕርግ ስሞች።

- **ሊቄ (የኔ ሊቅ)**

ይህ ማዕርግ በጥንት ዘመን በነገሥታቱ ይሰጥ እንደነበር ይነገራል። የዐራቱን ጉባኤያት የሐዲስ እና የብሉይ፣ ፍትሐ ነገሥት፣ መጽሐፈ መነኰሳት መዝሙረ ዳዊት ሊቅ።

- ሊቀ ማዕምራን — አጠቃላይ ዕውቀት ያለው።
- ሊቀ ጉባኤ — የብሉይ የሐዲስ መምህራን አለቃ ።
- ሊቀ ጠበብት — የጠቢባን በላይ ፣
- ሊቀ መዘምር — የመዘምራኑ አለቃ ወይም ሊቀጠበብት።

አጠቃላይ ዕውቀት ያለው ፤ የደጓ ያቋቋም ፣ የቅኔ፣ የቅዳሴ፣ የትርጓሜ መምህር የኾነ። በነዚህ በአንዱ የሰለጠነ።

- **ርዕሰ ደብር**

የደብሩ ራስ በግራ በኩል የሚቆም ፤ የደብሩ የጸዋትወ ዜማ ሊቅ መምህር።

- **መሪ ጌታ**

ያቋቋም የጽዋትወ ዜማ ይትበሀልን ጠብቆ የማሕሌትን ሥርዓት የሚያስከብር።

ቅዱስ (እፍዋተ መንግሥት) እንዲሁም ከወደ ምሥራቅ ከሚፈስ ውሃ አምጥተው ሰባት ዕጣን ጨምሮ ሰባት መነኰሳት መዝሙረ ዳዊት (መዝ 23) ከነቢያት እንዲሁም መሕልየ ሰሎሞንን ውዳሴ ማርያም ፤ አንቀጸ ብርሃን ፤ መልክአ ተክለ ሃይማኖት እየደገሙ ሰባት ሱባኤ ገብተው ይጸልያሉ ።

ሲነግሥም "ንዑስ አነ እም አኃውየ" ትርጉም "ከወንድሞቼ ይልቅ ትንሽ ነበርኩ" ከሚለው ጀምሮ "ወቀብዐኒ ቅብዐ ቅዱሰ" ትርጉም "ቅብዐ መንግሥትን ቀብቶ አነገሠኝ" እስከሚለው (መዝ.150 ፥1-4) በግእዙ ይደገማል ።

ካህናቱም ተቀብለው "ተከአወ ሞገስ እምከናፍሪከ" ትርጉም "ሞገስ ከከንፈሮችህ ፈሰሰ" ይሉና "ቅንት ሰይፈከ ኀያል ውስተ ሐቌከ" ትርጉም "ሰይፍኽን በወገብህ ታጠቅ" (መዝ. 44(45)፥3) እያሉ ባለወርቅ ሰገባ ሰይፍ ያስታጥቁታል።

ከዚያም "እርትዕ ተሠራሕ ወንገሥ" ትርጉም "አቅና ተከናወን ንገሥም" (ቁ. 3) ይሉና ወደ ቤተ መቅደስ ይገባሉ ። ከዚያም ጳጳሱ ቅብዓ መንግሥት የተቀመመውን ሜሮን በራሱ ላይ ያፈሱበታትል ። ስመ መንግሥት የሚኾን ስም እየተመረጠው ይቀርባል ። ዐዲሱ ስመ መንግሥቱ ይኩን ስምከ እገሌ ..... ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሥዩመ እግዚአብሔር ይሉታል።

የወርቅ ዘንግ ያስጨብጡታል ፤ የወርቅ ዘውድ ይደፋለታል ፥ በወርቅ ዙፋን ላይ ይቀመጣል ። ካህናቱ መንበርከ እግዚኦ ለዓለም ፤ ከርቤ ወቀንአት የሚለው ላይ ሲደርሱ (ቁ.6) ያቆማሉ ። ከዚያም ዲያቆኑ ወዐልዐልኩ ኅሩይየ እምሕዝብየ ይልና ምስባክ ይሰብካል።

ንቡረ እዱ (አለቃው) ከሉቃስ ወንጌል ብእሲ ክቡር ትርጉም "አንድ የከበረ ሰው መንግሥት ይዞ ሊመለስ ወደ ሩቅ አገር ኼደ" (ሉቃ. 19፥12) የሚለውን ያነባል ፤ ጳጳሱ "በእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር አምላክከ" ትርጉም "እግዚአብሔር አምላክህ የደስታ ዘይት ቀባህ" (መዝ.44(45)፥7) እያለ ይቀባዋል።

ይህም ዓይነቱ ሥርዓት ቤት ልጅ ስትዳር የዳቦ ስም እንደሚሰየምላት ኹሉ የንጉሡም በዚሁ ዓይነት ከብዙዎቹ ስሞች ተመርጦ ዕጣ ይወጣና ስመ መንግሥቱ ተሰጥቶት ይነግሣል ማለት ነው።
በዚህ ዓይነት ሲሰየም ኖሯል። በምሳሌነትም ከዚህ በታች ቀርበዋል።

| መጠሪያ ስም | ስመ መንግሥት |
|---|---|
| ዐፄ ይኩኖ አምላክ | ተስፋ ኢየሱስ (1263-1277 ዓ.ም) |
| ዐፄ አምደ ጽዮን | ገብረ መስቀል (1307-1336 ዓ.ም) |
| ዐፄ ንዋየ ማርያም | ውድም አስፈሬ (1364- 1374 ዓ.ም) |
| ዐፄ ዳዊት | ቆስጠንጢኖስ (1374 -1406 ዓ.ም) |
| ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ | ቆስጠንጢኖስ (1426-1460 ዓ.ም) |



| | |
|---|---|
| ዐፄ በእደ ማርያም | ዳዊት (1461 -1471 ዓ.ም) |
| ዐፄ እስክንድር | ቆስጠንጢኖስ (1471 - 1487 ዓ.ም) |
| ዐፄ ናዖድ | መርስኤ ሐዘን (1488 - 1500 ዓ.ም) |
| ዐፄ ልብነ ድንግል | ወናግ ሰገድ (1500 - 1533 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ገላውዴዎስ | አጥናፍ ሰገድ (1533- 1551 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ሚናስ | አድማስ ሰገድ (1551-1555 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ሠርጸ ድንግል | መለክ ሰገድ (1555-1589 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ፋሲል | ዓለም ሰገድ (1624 - 1660 ዓ.ም) |
| ዐፄ ዮሐንስ | አእላፍ ሰገድ (1660 - 1674 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ኢያሱ | አድያም ሰገድ (1674 -1698 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ተክለ ሃይማኖት | አብራክ ሰገድ (1698 -1700 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ቴዎፍሎስ | አጽራር ሰገድ (1700 -1704 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ዮስጦስ | ፀሐይ ሰገድ (1704 - 1708 ዓ.ም.) |
| ዐፄ በካፋ | መሢሕ ሰገድ (እስክንድር)(1713 - 23 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ዳዊት | አድባር ሰገድ |
| ዐፄ ኢያሱ | ብርሃን ሰገድ (1723 -1747 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ኢዮስያስ | አድያም ሰገድ (1747 -1761 ዓ.ም.) |
| ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ | ፍቅር ሰገድ (1772 - 1777 ዓ. ም.) |
| ሣህለ ሥላሴ | ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ (1832 -1840 ዓ.ም) |
| በሻህ ውረድ | ንጉሥ ኃይለ መለኮት (1840-1848 ዓ.ም) |
| ደጃዝማች ካሣ | ዐፄ ቴዎድሮስ (1848 -1860 ዓ.ም.) |
| ወግሹም ጎበዜ | ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ (1860 -1864 ዓ.ም) |
| በዝብዝ ካሣ | ዐፄ ዮሐንስ (1864 -1888 ዓ.ም.) |
| ምኒልክ | ዐፄ ምኒልክ (1881 -1906 ዓ.ም) |
| ልጅ ኢያሱ | ክፍለ ያዕቆብ (1906 -1909 ዓ.ም.) |
| አስካለ ማርያም | ንግሥት ዘውዲቱ (1909-1922 ዓ.ም.) |
| ደጃች ተፈሪ | ዐፄ ኃይለ ሥላሴ (1922-1967 ዓ.ም.) |



## (፭) አባ – የሚለው የማዕርግ እና የመጠሪያ ስም

አባ ከመጠሪያ ስም ጋር ተጨምሮ የሚነገር የክብር ተቀጽላ ነው ። በሃይማኖት መነኩሴ የኾነ በአባትነት የሚታይ አባ እገሌ ወይም ባጭሩ አባ በመባል ይጠራል ።

- አባ ጊዮርጊስ የጸሎት መጻሕፍትን የደረሱ (1417 ዓ. ም.)
- አባ ባሕርይ መዝሙረ ክርስቶስንና የኦሮሞን ታሪክ የጻፉ።(1528 ዓ.ም.)

በኹለተኛ ደረጃ ደግሞ አባ የሚለው ቅጽል በባህል ረገድ የመጀመሪያ ልጅ በኲር (አንጋፋ) ሲወለድ አባት የኾነው አባ እገሌ ወይም የእገሌ አባት እየተባለ ይጠራበታል። በተለይም በኦሮምኛ ባህል በመጀመሪያ ልጅ መጠራት የተለመደ ነው ። ሴት ልጅም ብትኾን ወንድ ልጅ የመጀመሪያ ከኾነ በልጁ ስም ይጠራል። ለምሳሌ <u>ሙሉ</u> ከኾነች <u>አባ ሙሉ</u> ። ይጠራል ማለት ነው ። እንዲሁም ደግሞ አባ ወራ ፤ የቤት ጌታ ፤ ባለቤት አሳዳሪ ማለት ነው ።
የጅማ ባለአባቶች አባ በሚለው ቅጽል ስም ይጠራሉ

- አባ ጅፋር - የጅፋር አባት

አባ ጅፋር በዐፄ ምኒልክ ዘመን የጅማ ባላባት ነበሩ ። የአባ ጀቢር ልጅ አባ ቢያ በአዲስ አበባ ዩኒበርሲቲ የሕግ ምሩቅ የኾኑ የኦርቶዶክስ ክርስትና አማኝ ነዋሪነታቸው በአሜሪካ ነው ።

- አባ ቢያ – ያገር አባት ፤ ዋና የአገር ተጠሪ አስተዳዳሪ ማለት ነው።
- አባ ገዲ
- አባ ዱላ
- አባ ገዳ

ሦስተኛው አባ ግን የኢትዮጵያውያን ነገሥታት፤ አርበኞች ፤ በፈረስ ጉግሥ ጫወታ ፈረሳቸው የሚጠራበት ስም አባ በማለት ቅጽል ተሰጥቷቸው ይጠሩበታል። ይህ የንጉሥ ጨዋታ ብዙ ጊዜ ይታይ የነበረው ከልደት ጊዜ ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር ። ለዚህ ለጥምቀት በዓል እና ለአስተርዮ እንደ ገና ጨዋታ ግጥሚያ ይኖር ነበር ። ጨዋታው ከግብ እስከ ግብ በመጋለብ ለጠላት ሳይገኝ መቅደም ። ከኋላው እየሮጠ በሽመል ሲሰበቅበት በጋሻው መከላከል ነበር ።
የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈረስ ግልቢያ ወይም የጉግሥ ልምድ ስለነበረው ለጦርነት ጊዜ ይረዳው ነበር። በፈረስ ግልቢያ ችሎታውና ኀይሉ ተማምኖ ጣሊያንን ድል ማድረግ ችሏል። <u>ለምሳሌ ፦</u>

- አባ ዲና ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ
- አባ ዳምጠው ንጉሥ ኀይለ መለኮት
- አባ ታጠቅ ዐፄ ቴዎድሮስ
- አባ በዝብዝ ዐፄ ዮሐንስ
- አባ ዳኘው ዐፄ ምኒልክ ነበሩ



- አባ ጠቅል ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ነበሩ

ዐርበኞች

- አባ ጉራቻ ደጃዝማች ወልደሚካኤል ጉዲሳ
- አባ ይትረፍ ራስ አባተ
- አባ ነጋ ራስ ዐሉላ ምርጫው
- አባ መቻል ሪታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ
- አባ ነፍሶ ደጃች ባልቻ ፤ ለነፍሳቸው ይመጸውቱ ነበር።

## (፪) ነገሥታት ማዕርግ ሲሰጡ የሚሰይሙት ስሞች።

ይህ የሹመት ስም ከጥንት ጀምሮ የነበረ ነው። በቅርብ ዓመታት ወዲህ የፊውዳሎች ስም ነው እየተባለ ይኰነናል ። ነገር ግን በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተገለጸው የንግሥት ህንደኬ በጅሮንድ እንደነበረ ይታወቃል (የሐ. ሥራ.8፥26)።

- ዐፄ

የማይወቀስ የማይከሰስ የሕዝብ አባት (ንጉሠ ነገሥት) ሥልጣኑን የሚያገኘው የዳዊት ወንበር የተባለው ላይ ተቀምጦ ከተጠመቀ በኋላ ነው።

- መርዕድ (ግእ) (መርድ)

ደባትሪሁ ዘነድ ወሠረገላሁ መርዕድ።
ትርጕም ፤ የሚያነቀጠቅጥ ጽምጹ የሚያስፈራ (ዕዝ. ሉቃ 1፥19)።
የከበሬታ ስም ከንጉሥ በታች ከራሶች በላይ አልጋ ወራሽ የሚጠራበ ነው።

- ልዑል

ተለዓለ ከፍ ብፍ ያለ ማለት ሲኾን። ከፍተኛ ማዕረግ ነው።

- ልዕልት ከፍ ከፍ ያለች የንጉሣውያን ቤተሰብ ሴት ልጅ።
- ራስ የበላይ ጦር አለቃ (ጀነራል) ማለት ነው።
- ቢቶደድ ጠቅላይ ሚኒስትር። (በልዩ ኹኔታ የተወደደ)
- አፈ ንጉሥ የፍርድ ሚኒስትር።
- ጸሐፌ ትእዛዝ የጽሕፈት ሚኒስቲር።
- አዛዥ የግቢ ሚኒስትር ።
- በጅሮንድ የገንዘብ ሚኒስትር።

(በጆሮ ወእድ – በጆሮና በእጅ?) ምስጢርን በጆሮ ነጋሪና የግምጃ ቤትን ቁልፍ አዛዥ ነው ። ለሴት ንግሥት በጆሮ ወንድ የሚኾነው ጃንደረባ ነው።

- ነጋድራስ የንግድ ሚኒስትር (ነጋ ድረስ?)።
- ከንቲባ የከተማ መዘጋጃ ቤት ሹም (ካንት ይባዕ?)።



## መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት

በአጠቃላይ ይዘቱ በጣም ጥሩ ነው። ሐሳቡም ከዚህ በፊት ያልተዳሰሰና በዚህ ርዕስ መጽሐፍ ያልተዘጋጀ ስለኾነ ዝግጅቱ የተዋጣለት ነው።

ኾኖም መጽሐፉ ብዙ ወራትና ዓመታትን መስዋዕትነት ያስከፈለ መኾኑ የታወቀ ቢኾንም ለመጭውም ኾነ ለአለው ትውልድ ፈር ቀዳጅ መመራመሪያ መንገዱን እንደሚከፍት ጥርጥር የለውም። ዕውቀት በዶማ እንደሚቆፈር ጎሮ በበሬ እንደሚታረስ ማሳ ሳይኾን ከአንዱ ጭንቅላት ወደ ሌላው ጭንቅላት የሚተላለፍ የብርሃን ፋና ነው። ስለዚህ አንዱ ከሌላው አይቶና ሰምቶ የሚገበየው ሀብት ስለኾነ በጸሐፊው መልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት የተዘጋጀው መጽሐፍ ጠቃሚነቱ የጎላ ከመኾኑም ለሀገርም ኾነ ለወገንም ለትምህርት ቤት ማስተማሪያ ስለሚጠቅም ጸሐፊው የመጀመሪያ መጽሐፋቸው የመጨረሻ እንደማይኾን ባለሙሉ ተስፋ በመኾን ሌላም አዘጋጅተው እንዲያቀርቡልን ብርታቱንና ጽናቱን እንዲሰጣቸው ያምላክ ፈቃድ ይኹን።

አባ ማቴዎስ
የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና
የዋግ ሕምራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

ብዙ ወላጆች ለልጆቻቸው ስም ለማውጣት ሲጨነቁ ማየት የተለመደ ኹኔታ ቢኾንም ከዘመዶቻቸው የራቁ ወጣት ወላጆች ደግሞ ጭንቀታቸው የበዛ ነው። ለዚህም አንዱ ምክንያት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ስለ ስም አወጣጥና ትርጉም የሚገልጽ ጽሑፍ እምብዛም ባለመኖሩ ነው።
ይህ በመልአከ ብርሃን ብርሃኑ ብሥራት የተዘጋጀው መጽሐፍ በዚህ ረገድ በአገራችን ፈር ቀዳጅና ወቅታዊ ሲኾን፤ በየትኛውም የዓለም ክፍል ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚያስፈልጋቸው ነው ብዬ አምናለሁ። መጽሐፉ ከያዛቸው የስሞች ዝርዝር በተጨማሪ የስያሜዎቹ አከፋፈልና ትርጉም እጅግ ጠቃሚ ኾኖ አግኝቼዋለሁ። በመኾኑም በዘርፉ ምርምር ለሚያደርጉ ሰዎችም ጥሩ መረጃ ሰጪ የሚኾን መጽሐፍ ነው።

ሰሙ ምትኩ (ዶ/ር)
አ.አ ዩኒቨርስቲ ረዳት ፕሮፌሰር

**ቀድሞ የወጣ**
- ኑሮና ክርስትና በአሜሪካ

**ወደፊት የሚወጡ**
- ፍኖተ ኦርቶዶክስ ዘተዋሕዶ
- ኑሮና ክርስትና በብሪታንያ

ኤች ዋይ ማተሚያ ቤት
+ 251-11-553 90 95

ዋጋ 25 ብር
£ 10 $ 15